27

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ
# ክትትል ጥናት (ቤተኑክ-ጥናት)

## *የሙከራ ጥናት (1995)*

**Core Welfare Indicators Questionnaire (CWIQ)**

*Pilot Survey (2003)*

## *የመረጃ አሰባሰብ መመሪያ*

አዲስ አበባ
ሰኔ 1995

# ማ ው ጫ


| ተ.ቁ. | ር እ ስ ት | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | አጠቃላይ መመሪያ | 1 |
| 2 | የጥናቱ ዓላማዎች | 3 |
| 3 | ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ርዕሶች | 4 |
| 4 | ጽንሰ ሀሳቦችና ፍቺዎቻቸው | 5 |
| 5 | የቤተሰቦች የኑሮ ሁኔታ ክትትል መጠይቅ አሞላል አጠቃላይ መመሪያ | 7 |
| 6 | ጥናቱ የሚያቅፋቸው ቤተሰቦች አመራረጥ | 10 |
| 7 | ክፍል፡ ሀ- የመጠይቁ ዝርዝር መረጃ | 11 |
| 8 | ክፍል፡ ለ- የቤተሰብ አባላት ዝርዝር እና አጠቃላይ መመሪያ | 14 |
| 9 | ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር | 19 |
| 10 | ክፍል፡ ሐ- ትምህርት | 24 |
| 11 | ክፍል፡ መ- ጤና | 31 |
| 12 | ክፍል፡ ሠ- የሥራ ሁኔታ | 38 |
| 13 | ክፍል፡ ረ- የቤተሰቡ የቋሚ ንብረት ሁኔታ | 50 |
| 14 | ክፍል፡ ቀ- ቤተሰቡ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች | 58 |
| 15 | ክፍል፡ በ- የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት | 62 |
| 16 | ክፍል፡ ተ- ዕድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት | 64 |
| 17 | ክፍል፡ ቸ- የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አጠቃቀምና እርካታ | 69 |

# የ1995 ዓ.ም. የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል (ቤተኑክ) የሙከራ ጥናት የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ

## 1. አጠቃላይ መመሪያ

### 1.1. የመረጃ ሰብሳቢው ተግባርና ኃላፊነት

በተመረጡ ወረዳዎች ተመድቦ የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ ክትትል የሙከራ ጥናት የሚሰማራ መረጃ ሰብሳቢ ለጥናቱ ሥራ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። ስለሆነም መረጃ ሰብሳቢው የመረጃ አሰባሰቡን ተግባር በቅንነት፣ በታማኝነትና በታታሪነት ማከናወን ይገባዋል። መረጃ ሰብሳቢው ከተመደበበት ቦታ ነዋሪ ከሆነ ሕዝብ ጋር ተግባብቶ ባህሉን አክብሮ የመረጃ አሰባሰቡንተግባር ከማከናወኑም በላይ የሕዝቡን ድጋፍና ትብብር ለማግኘት ከአስነዋሪ ድርጊቶች ሁሉ መራቅ ይኖርበታል። በተጨማሪም ማንኛውም መረጃ ሰብሳቢ በሥራው ወቅት ከሥራው ጋር ግንኙነት በሌላቸው ተግባራት (መነገድ፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ቅስቀሳዎችና የመሳሰሉት) ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መሰማራት አጥብቆ የተከለከለ ስለሆነ ይህንን አውቆ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

መረጃ ሰብሳቢው ተግባሩን ለማካሄድ ወደ ቤተሰቡ በሚደርስበት ወቅት ሰላምታ በመስጠት እራሱን ማስተዋወቅ፣ ስለ መጣበት ዓላማ መግለጽና ለጥናቱ ቀና ትብብር የሚያገኝበት መንገድማመቻቸት ይኖርበታል። ለጥናቱ መረጃ ስብሰባ ሥራ የሚጠየቁ ጥያቄዎች በመመሪያው መሠረት መሆን ያለበት መሆኑን በመገንዘብ አግባብ የሌለውን ጥያቄ መጠየቅ አይኖርበትም። ሥራውንም ካጠናቀቀ በኋላ ቤተሰቡን አመስግኖ መሰናበት ይኖርበታል። በአጠቃላይ ሥራው ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ታታሪ፣ ትሁት፣ ቀልጣፋና ተግባቢ መሆን ያስፈልጋል።

መረጃ ሰብሳቢው ተግባሩን ለማከናወን የተለያዩ ቅጾችንና ጥያቄዎችን በእርጋታ በማጤን በመሙላት ተገቢውን መልስ ሲያጠቁር በጥንቃቄና መጠይቁን በመመሪያው ላይ በማስደገፍ መሆን አለበት። እንደዚሁም ያጠቆራቸው ጥያቄዎች ሁሉ በመመርመር አስፈላጊውን ዕርማት ማድረግ ያለበት ከመሆኑም በላይ ካስፈለገ ወደ ቤተሰቡም በመመለስ በስህተት የጠቆሩ፣ የማይመስሉ፣ እርስ በእርስ የማይጣጣሙ፣ ... ወዘተ ምላሾችን ማስተካከል አለበት። ለጥናቱ የሚሰጡትን ዶክመንቶችና ሌሎች ዕቃዎች በጥንቃቄ መያዝና በመረጃ ስብሰባው ወቅት የሚሰበስቡትን መረጃዎች በሚስጥር መጠበቅና ከተቆጣጣሪውና ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን ሠራተኞች (መታወቂያ በመጠየቅ) በስተቀር ለማንም ግለሰብ ማሳየት አይገባውም። ከዚህም ሌላ በሥራ ወቅት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ እንደ የመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ የሕፃናትሚዛን፣ ሜትር እና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ከመረጃ ሰብሳቢው ሊለዩ አይገባቸውም።

መረጃ ሰብሳቢው ከቤተሰቡ ዘንድ በመሄድ የቤተሰቡን ኃላፊና ቢቻል የቤተሰቡን አባላት በማነጋገር በቅፆቹ የተመለከቱትን ጥያቄዎች እየተረዳዱ እንዲመልሱ ማድረግ ይገባዋል።

## 1.2. የአፈፃፀም ቅደም ተከተል፣ አስፈላጊ ዶኩመንቶችና ቁሳቁሶች

### 1.2.1. የአፈፃፀም ቅደም ተከተል፦

የቤተቦችን የኑሮ ሁኔታ ክትትል የሙከራ ጥናት መጠይቅ ለመሙላት (መረጃ ለመሰብሰብ) የሚሰማሩ መረጃ ሰብሳቢዎች ስራቸውን በሚከተለው ቅደም ተከተል ያከናውናሉ።

ሀ. ስልጠናው እንደተጠናቀቀ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ዶክመንቶችና እቃዎች (መጠይቆች፣ መመሪያዎች፣ የሕፃናት ክብደት መለኪያ ሚዛን፣ ቁመትና ርዝመት መለኪያ ሜትርና የመሳሰሉት) ቆጥሮ ትክክለኝነታቸውን በማረጋገጥ በጥንቃቄ መረከብ፣

ለ. ለአንድ ቤተሰብ የተሞላውን መጠይቅ በመመርመር ያልተሟሉ ዓምዶችን ወይም ጥያቄዎችን በመለየት የዕለቱ ዕለት በተቻለ መጠን ከቤተሰቡ ሳይርቅ ወደ ቤተሰቡ በመመለስ ማሟላትና አስቸጋሪ ጉዳይ ካጋጠመ ተቆጣጣሪውን በማማከር የዕለቱ ዕለት መፍትሄ መሻት፣

ሐ. በሥራው ወቅት ችግር ሲያጋጥም ወዲያውኑ ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ መፍትሄ ማግኘትና የተሰጠውን የመፍትሄ ሐሳብ መመዝገብ፣

መ. ሥራው በትክክል ተሰርቶ መጠናቀቁን ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን ካረጋገጡ በኋላ የተጠናቀቁ መጠይቆችን ለተቆጣጣሪው ማስረከብ።

ሠ. ተቆጣጣሪው የድጋሚ መጠይቆችንና የተግባር ሥራዎችን ሲያከናውን አብሮ በመሄድ መታረም ያለበት ካለ እርማት ማድረግ።

ረ. ያጋጠሙ ችግሮችና አፈታታቸውን በሚመለከት ከቡድኑ ጋር በመቀናጀት ዕለታዊ ዘገባ (የየቀኑን ሪፖርት) አዘጋጅቶ ለተቆጣጣሪው ማስረከብ።

### 1.2.2. ለሥራው የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችና ዕቃዎች

ለሥራው የሚያስፈልጉ ዶክመንቶችና ዕቃዎች፦

ሀ. የመረጃ ሰብሳቢው መመሪያ፣

ለ. የተጠረዘ ባለ 9 ገጽ የቤተሰቦች የኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት መጠይቅ በተመረጡት ቤተሰቦች ብዛት፣

ሐ. የጽህፈት መሳሪያዎችና ቦርሳ፣

መ. ለጥናቱ የተመረጡ ቤተሰቦች ዝርዝር፣

ሠ. የሕፃናት ክብደትና መለኪያ ሚዛንና ቁመት መለኪያ የጣውላ ላይ ሜትር፣

ረ. መረጃ ሰብሳቢ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ መሆኑን የሚገልፅ የመታወቂያ ወረቀት፤

ሰ. ለቀበሌ/ገበሬ ማኅበራት የሚፃፍ የትብብር ደብዳቤ (ካለ) ናቸው።

2. <u>የጥናቱ ዓላማዎች</u፡- የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

እጠቃላይ ዓላማዎች

1. በአገሪቱ ውስጥ ለሚታየው የድህነት ሁኔታ መሠረታዊና ጠቃሚ መረጃዎችን በማሰባሰብ ወደፊት የሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦችን ለመከታተልና ለማጥናት፤

2. ለአጭርና ለመካከለኛ ጊዜ የታቀዱ አዳዲስ ፖሊሲዎች በቤተሰቦች የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ደህንነት ላይ የሚያስከትሉትን ውጤት ለመገምገም፤

3. ድህነትን ለመቀነስና ለማጥፋት እንዲቻል በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮረ ዘላቂ የሆነ የመረጃ አሰባሰብ ስልት በመቀየስ አስተማማኝ መረጃ ለማቅረብ፤

4. በአገሪቱ ያለውን የትምህርት ስርጭት ስፋት፤ የትምህርት ቤቶች በቅርብ መገኘት፤ የተማሪዎች ትምህርት ማቋረጥና ምክንያቱ፤ ለማወቅ የሚያስችል የመማር ማስተማር ሂደት የሚያደናቅፉ ችግሮች መረጃ ለማግኘት፤

5. በእርግዝና ወቅት የሚደረግ የህክምና ክትትል ሁኔታ ለማወቅ፤

6. ሰዎች በታመሙ ጊዜ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት የት እንደሚሄዱ ወይም ምን እንደሚያደርጉ ለማወቅና ታመው የሕክምና እርዳታ ያላገኙበት ምክንያት ለማወቅ የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት፤

7. ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በሚመለከት ሕዝቡ ያለውን አስተያየት ለመግለፅ ከመርዳቱም በላይ በአሁኑ ወቅት ለሕዝቡ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ከሕዝቡ ፍላጎት ጋር ምን ያህል እንደሚመጣጠን ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት።

8. በሃገሪቱ ያለው የሥራ ሁኔታና የሥራ እጦ ሁኔታ የሚያመለክቱ ጠቃሚ መረጃዎች ለማግኘት፤

9. የቤተሰቦች ቋሚ ንብረቶች ሁኔታ ለመገምገም የሚያስችሉ ጠቃሚ መረጃዎች ለማግኘት፤

10. የቤተሰቦች የመኖሪያ ሁኔታ፤ ቤተሰቦች ስለሚጠቀሙባቸው ግልጋሎቶች (የንፁህ ውሃ አቅርቦት፣ የመብራት፣ የማገዶ፣ የመፀዳጃ ... ወዘተ) እና የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ርቀት (የውሃ፣ የት/ቤት፣ የሕክምና መስጫ ተቋም፣ የመንገድ፣ የመገናኛና ትራንስፖርት፣ የወፍጮ) ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለማጠናቀር፣

11. ቤተሰቦች እያጋጠማቸው ያለውን አስደንጋጭ ችግር ምን እንደሆነና በምን መልክ እንደሚፈቱት የሚጠቁም መረጃ ለማግኘት፣

12. የሕፃናት ክብደት፣ ቁመትና ዕድሜ በማገናዘብ የአስተዳደጋቸውን ሁኔታ ሊጠቁም የሚችል መረጃ ለማግኘትና እንዲሁም የሕፃናትን የክትባት ሁኔታ (ፀር ፮) በመገምገም ክትባት የሚስፋፋበት መንገድ ለመቀየስ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ናቸው።

ስለሆነም እነዚህን ጠቋሚ በአገር አቀፍ ደረጃ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል።

## 3. ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ርዕሶች

ጥናቱ የሚያተኩርባቸው ርዕሶች በአስር ዋና ዋና ክፍሎች (A - J) በተከፋፈሉ /መጠይቆች/ ቃና የተጠቃለሉ ሲሆን እያንዳንዱ ክፍል የሚያመለክተው ርዕስ የሚከተለው ነው።

**Section A- INTERVIEW INFORMATION**

ክፍል ሀ ስለ ቃለ መጠይቁ ክንውን መረጃ ይህ ክፍል የሚመለከተው የተመረጠው ቤተሰብ አድራሻ፣ ቃለ መጠይቁ የተጀመረበት ቀንና ሰዓት፣ የተገኘው ውጤት፣ ... ወዘተ ነው።

**Section B- LIST OF HOUSEHOLD MEMBERS**

ክፍል ለ - የቤተሰብ አባላት ዝርዝር

**Section C- EDUCATION**

ክፍል ሐ - የትምህርት ሁኔታ

**Section D- HEALTH**

ክፍል መ - የጤና ሁኔታ

**Section E- EMPLOYMENT**

ክፍል ሠ - የሥራ ሁኔታ

**Section F- HOUSEHOLD ASSETS**

ክፍል ረ - የቤተሰብ ቋሚ ንብረቶች

**Section G- HOUSEHOLD AMENITIES**

ክፍል ቀ - ቤተሰቡ ስለሚጠቀምበት የቤትና የውጭ ግልጋሎቶች

**Section H- WELFARE**

ክፍል በ - የቤተሰቦች አጠቃላይ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት ጠቋሚዎች

**Section I- CHILDREN UNDER 5**

ክፍል ተ- ከ5 ዓመት ዕድሜ በታች ስላሉ ህፃናት የጤናና አመጋገብ ሁኔታ

**Section J:- USE AND SATISFACTION WITH FACILITIES AND SERVICES**

ክፍል ቸ:- በአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አጠቃቀምና እርካታ

## 4. ፅንሰ ሀሳቦችና ፍችዎቻቸው:-

ሀ. ቤተሰብ:- ቤተሰብ ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ውስጥ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድ ማዕድቤት አብስለው በአንድነት የሚመገቡ ሰዎችን ያጠቃልላል:: የቤተሰብ አባላት በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱትንና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል:: በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱት ባል፣ ሚስት፣ ልጆች፣ የባል/የሚስት ወላጆች፣ እህት፣ ወንድም፣ አጎት፣ አክስት ... ወዘተ ናቸው:: በሥጋ ወይም በጋብቻ የማይዛመዱ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ለምሣሌ በቤት ሠራተኛነት፣ በዘበኝነት የሚያገለግሉ ግለሰቦች ከቤተሰቡ ጋር አብረው የሚኖሩና የሚመገቡ ከሆነ እንደ ቤተሰብ አባል ይቆጠራሉ::

የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል:: ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል፣ ወይም ሌሎች ሰዎች እንደ ዘበኞች፣ ጥገኞች ... ወዘተ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚኖሩና በአንድነት የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ:: ነገር ግን ጥናቱ ከሚከናወንበት ዕለት በፊት ቤተሰቡን ትቶ በአንግድነት ወደ ሌላ ቤተሰብ በመሔድ እዚያ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ከተቀመጠ አሁን ለሚገኝበት ቤተሰብ እንግዳ መሆኑ ቀርቶ ለቤተሰቡ አባል ይሆናል ማለት ነው::

ጋብቻው በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልን፣ ሚስትን፣ ልጆችን፣ የጉዲፈቻ ልጆችን፣ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን (የቤት ሠራተኞች … ወዘተ) ሊያጠቃልል ይችላል። ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ (አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ካሉት) የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው … ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የማይኖሩና ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የማይበሉ ከሆነ፣ ባልየው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት (አንጋፋ) ሚስቱ ጋር እንደ አንድ የቤተሰብ አባል ተቆጥሮ ሌሎቹ የሰውየው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ እንዳላቸው ሆኖ መቆጠር አለባቸው። ይህም የሚሆነው ሰውየው የቤተሰብ አባልነት መመዘኛ የሚያሟላ ሲሆን ነው።

ለ. <u>መደበኛ የቤተሰብ አባል፡-</u> አንድ ሰው መደበኛ የቤተሰብ አባል ነው የሚባለው ቢያንስ ስድስት ወር ሙሉ ያለማቋረጥ ከቤተሰብ ጋር የኖረ እንደሆነ ነው። ከቤተሰቡ ጋር ለዘለቄታው ለመኖር የመጡ ሁሉ ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል ይቆጠራሉ። ከስድስት ወር በታች ከቤተሰቡ ለጊዜው ተለይተው የቆዩ የቤተሰብ አባላት እንደመደበኛ የቤተሰቡ አባል መቆጠር አለባቸው፣ ነገር ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ከሄዱ ስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው፣ ወይም ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት አቅደው የሄዱ ከቤተሰቡ ከወጡ ስድስት ወር ባይሞላቸውም እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም።

## <u>የሚከተሉት የቤተሰብ አባላት እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል መቆጠር ይኖርባቸዋል።</u>

1. በጥናቱ ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር ቢያንስ ለስድስት ወር የቆዩ።

2. ከቤተሰቡ ጋር መኖር ከጀመሩ ስድስት ወር ባይሞላቸውም ከቤተሰቡ ጋር ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ለመቆየት ዕቅድ ያላቸው ሁሉ፡- ለምሣሌ ባል አግብታ ከወላጆችዋ ቤት ወደ ባልዋ የሄደች ሴት ስድስት ወር ባይሞላትም የባሏ ቤተሰብ መደበኛ አባል ትሆናለች ማለት ነው። እንዲሁም ሥራ አግኝቶ/ታ ለዘለቄታው ለመኖር ወደ ሌላ ቤተሰብ የሄደ/ች ስድስት ወር ባይሞላውም/ትም በጥናቱ ወቅት የተገኘበት/ችበት ቤተሰብ አባል ይሆናል/ትሆናለች።

3. የቤት ሠራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ከቤተሰቡ ጋር የሚያድሩና ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሁሉ።

4. በጥናቱ ጊዜ ከስድስት ወር ላነሰ ከቤተሰቡ ለጊዜው የተለዩ፣ ለምሣሌ በዕረፍት ላይ ያሉ፣ በዓመት በዓል ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ፣ ሆስፒታል የገቡ፣ ዘመድ ለመጠየቅ የሄዱና ከሥራቸው ጋር በተያያዘ ጉዳይ ላይ ያሉትን አባላት ሁሉ ያጠቃልላል።

5. ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የሌላቸውና በጥናቱ ወቅት ከቤተሰቡ ጋር የሚኖሩ አባላት ሁሉ፤ ለምሣሌ በተለያዩ ቤቶች እያተያየሩ ለሚኖሩና መደበኛ መኖሪያ የሌላቸው ግለሰቦች በጥናቱ ወቅት በሚገኙበት ቤተሰብ እንደ መደበኛ አባል ተቆጥረው ይመዘገባሉ።

6. <u>ተማሪዎች፡-</u> ከቤተሰቦቻቸው፤ ከወላጆቻቸው፤ ከመደበኛ የመኖሪያ ሥፍራቸው ተለይተው በመደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆች፣ በዩኒቨርስቲዎች ... ወዘተ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ ተማሪዎች በሙሉ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት አካባቢ መደበኛነዋሪዎች ሆነው መመዝገብ አለባቸው። በአዳሪ ት/ቤት የሚማሩ ተማሪዎች እንዲሁም ከወላጆቻቸው ተለይተው ቤት ተከራይተው ወይም ከዘመድ ተጠግተው እየኖሩ የሚማሩ ተማሪዎች ምንም እንኳን በየሳምንቱ ወይም በየአሥራ አምስት ቀን ስንቅ ለማምጣት ወይም ወላጆቻቸውን ለመጠየቅ ወደ ቤተሰቦቻቸው ቢሄዱም እንደ መደበኛ የቤተሰብ አባል የሚታሰቡት በሚኖሩበት አካባቢ እንጂ በወላጆቻቸው ቤት አይደለም። ነገር ግን ከመደበኛ መኖሪያቸው (ከቤታቸው) በየቀኑ ወደ ትምህርት ቤቶች እየተመላለሱ የሚማሩ ተማሪዎች ሁሉ የሚኖሩበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ሆነው መመዝገብ አለባቸው።

ሐ. <u>የቤተሰብ ኃላፊ፡-</u> «የቤተሰብ ኃላፊ» ማለት የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሆነ ወንድ/ሴት በቤተሰቡ አባላት እንደ ኃላፊ የሚቆጠር/የሚታይ ነው። ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉት ሰው ሚስቶቹ በተለያዩ ቤተሰብ የሚኖሩ ከሆነ እሱ የቤተሰቡ ኃላፊ ሆኖ የሚመዘገበው አሁን በሕይወት ካሉት ውስጥ በቅድሚያ ካገባት/አንጋፋ ሚስቱ ጋር ይሆናል። ሌሎች ሚስቶች ግን የየራሳቸውን ቤተሰብ ኃላፊ(አባል) ሊሆኑ ይችላሉ። ይህም የሚሆነው ባልየው በሚያሻማ መልኩ ከሁሉም ሚስቶቹ ጋር የሚኖር ከሆነ ነው።

## 5. <u>የቤተሰቦች የኑሮ ሁኔታ ክትትል መጠይቅ አሞላል አጠቃላይ መመሪያ</u>


ይህ መጠይቅ ከዚህ በፊት በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ሲከናወኑ ከቆዩት የተለያዩ ጥናቶች ሲዘጋጁ ከነበሩት መጠይቆች በእጅጉ የተለየ ነው።

ይኸውም መጠይቁ የሚሞላው የተሰጠውን (የሚገኘውን) መልስ በመመዝገብ ወይም ለተያቄው ከሚዘጋጁ አማራጭ መልሶች መካከል ትክክለኛውን መልስ በመክበብ አልያም የመለያ ቁጥሩን (ኮድ) ለጥያቄው በሚሰጠው ክፍት ቦታ ወይም ካርድ ኮለም ውስጥ በመመዝገብ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛውን መልስ በተገቢው ቦታ በማስፈርና በማጥቆር በመሆኑ ነው።

አብዛኛው ሰው እንዲህ ዓይነት አሰራር የሚያውቀው በ12ኛው ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወቅት (በቅርቡ በ10ኛ ክፍል) ብቻ ነው። በስራ ላይ እንዲውል የተዘጋጀው የኑሮ ሁኔታ ክትትል ጥናት መጠይቅ አሞላልም ልክ እንደ 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና የመልስ መስጫ

ወረቀት በጥንቃቄ በማጥቆር ይሆናል:: በመሆኑም መጀመሪያ ቢተሰቡን ወይም የቤተሰቡ አባል ለሚቀርብለት ጥያቄ የሰጠውን መልስ በትንሹ ምልክት በማድረግ መያዝ፣ ለጥያቄው ከተሰጡት መልሶች ጋር ማዛመድና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ከዚያም የተሰጠው መልስ በመጠይቁ ስር ወይም ጎን ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ክብ ነገር (ክብ ነገሮች) በጥንቃቄ ማጥቆር ያስፈልጋል:: መልሱ በማጥቆር የማይመለስ ከሆነ ትክክለኛውን አሃዝ በተሰጠው ክፍት ቦታ በጥንቃቄና "የቁም ጽሑፍ" በሚባለው ዓይነት ማስፈር ያስፈልጋል::

ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት መረጃ የተሞላባቸው መጠይቆች በሰው አመካይነት የዳታ ኢንትሪ ሥራ (መረጃ ወደ ኮምፒውተር የማስገባት ተግባር) የሚከናወንላቸው ሳይሆኑ Scaner የሚባለው መሳሪያ በመጠቀም እንደ ፎቶ ኮፒ አሰራር ወይም እንደ ፎቶ ግራፍ በቀጥታ እንዲነሱ በማድረግ የሚከናወን በመሆኑ ነው:: በዚህ መሠረት የሚከተሉትን ምሳሌዎች ልብ ብሎ ማስተዋል ያስፈልጋል::





ከላይ እንደሚታየው በትክክል የጠቆረው በ6ኛ ተራ ቁጥር ያለው ብቻ ነው:: ምክንያቱም

1. በተራ ቁጥር 1 እና 2 ያሉት በመመሪያው መሠረት የጠቆሩ ሳይሆኑ የ"x" እና የ"✓" ምልክት የተደረገባቸው ናቸው::
2. በተራ ቁጥር 3 ያለው በትክክል የጠቆረ ቢመስልም የማጥቆሩ ተግባር የተከናወነው ከክቡ ውጭ ጭምር በመሆኑ ነው::
3. በተራ ቁጥር 4 ያለው በትክክል የጠቆረ ቢመስልም የጭረት ምልክት ይታይበታል::
4. በተራ ቁጥር 5 ያለው በትክክል የጠቆረ ቢመስልም በቀኝ በኩል ሾጣጣ ቅርፅ እንዲኖረው በመደረጉ ነው::
5. በተራ ቁጥር 7 ያለው ሙሉ በሙሉ ክቡ ነገር ባለመጥቆሩ፣
6. በተራ ቁጥር 8 ያለው ከክቡ መሐል ሳይጠቁር የቀረ ክፍተት ያለው ሲሆን፣
7. በተራ ቁጥር 9 ያለው ክብ ደግሞ ሙሉ በሙሉ የተሸፈነ ቢመስልም የጠቆረው በስሱ በመሆኑ ነው::

በመሆኑም መሳሪያው ከእነዚህ መካከል በ6ኛ ተራ ቁጥር የተገለፀውን ብቻ በትክክል ያነባል:: ሌሎች የተለያዩ ቅጥያዎች ወይም ያልገጠሙ ዕሑፎች በመሆናቸው በትክክል አያነባቸውም

ከነዚህ ምሳሌዎች የምንረዳው ቁም ነገር ቢኖር ያለምንም ማዛነፍ በጥንቃቄ ማጥቆርና መፃፍ የግድ መሆኑን ነው::

ለ. የቁጥሮች አፃፃፍ ምሳሌ



ስለሆነም መረጃው የስካነር መሳሪያ ተጠቅሞ ለማተንበር እንዲቻል መጠይቁ በከፍተኛ ጥንቃቄ መሞላት (መጠቆር) ይኖርበታል። ይህንን ተግባር በሚገባ ለማከናወን ሁለት ደረጃ ያለው የአሠራር ዘዴ መጠቀም ያስፈልጋል።

1. በቃለ መጠይቁ ወቅት

መረጃውን በትክክል ለመሙላትም ሆነ ለማጥቆር እርሳስ መጠቀም ያስፈልጋል። በተጨማሪም እያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ ላጲስ ከእጁ መለየት የለበትም። በመጀመሪያ ደረጃ የተገኘውን መልስ በየጥያቄው ስር ባሉት ክፍት ቦታዎች ማስፈር ያስፈልጋል። ከዚያም ቁጥሮቹ በትክክል ለማንበብ ወይም ለመፃፍ አማካይ በሆነ ቦታ ላይ በማስቀመጥ በትክክለኛ ቦታቸው ላይ መሙላት/ማጥቆር ያስፈልጋል።

2. መጠይቁ መጠናቀቁን ማረጋገጥ

የተሰጠውን መልስ በትክክለኛው ቦታ መስፈሩንና ተገቢው ክብ መጥቆሩን ለማረጋገጥ እንዲቻል እንደገና መጠይቁን አንድ በአንድ ማገናዘብ ያስፍልጋል። ከዚህም ሌላ የጠቆሩ ክቦች በትክክል መጥቆራቸውን፣ መጠይቁ ንፁህ መሆኑን ማለትም የማያስፈልጉ ምልክቶች የሌሉት መሆኑንና በመጠይቁ ዳርና ዳር ያሉ ቦታዎች ምልክት ከተደረገባቸው የስካኒንግ መሳሪያው ስለማይቀበል ምንም ዓይነት ምልክትም ሆነ የመቆሸሽ፣ የመተጣጠፍ ... ወዘተ አለመኖሩ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ከአንድ በላይ መልስ ማጥቆር ከሚቻልባቸው ጥያቄዎች ውጭ ሌሎቹ በሙሉ አንድ መልስ ብቻ እንደተጠቆረባቸው ደግሞ ደጋግሞ ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

6. ## ጥናቱ የሚያቅፋቸው ቤተሰቦች አመራረጥ፡- በጥናቱ የሚታቀፉ ቤተሰቦች ዝርዝር በቅድሚያ ተመርጠው ይሰጣሉ፡፡

## ዝርዝር የአሞላል መመሪያ

SECTION A- INTERVIEW INFORMATION

ክፍል ሀ፡- የመጠይቁ ዝርዝር መረጃ

Q.1 REGION

ጥ.1 ክልል

ጥናቱ የሚካሄድበት ክልል ስም ይፃፋል፡፡

Q.2 ZONE

ጥ.2 ዞን

ጥናቱ የሚካሄድበት ዞን ስም ይፃፋል፡፡

Q.3 WOREDA

ጥ.3 ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ ስም (ቁጥር) ይፃፋል፡፡

Q.4 TOWN

ጥ.4 ከተማ

ጥናቱ የሚካሄድበት ከተማ ስም ይፃፋል፡፡

Q.5 HIGHER/WOREDA

ጥ.5 ከፍተኛ/ወረዳ

ጥናቱ የሚካሄድበት ከፍተኛ/ወረዳ ቁጥር (ስም) ይፃፋል፡፡

Q.6 KEBELE/FA

ጥ.6 ቀበሌ/ገበሬ ማኅበር

ጥናቱ የሚካሄድበት ቀበሌ ወይም ገበሬ ማኅበር ቁጥር (ስም) ይፃፋል፡፡

Q.7 NAME OF HEAD OF HOUSEHOLD

ጥ.7 የቤተሰብ ኃላፊው ስም

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ኃላፊው ማን እንደሆነ ተጠይቆ ሙሉ ስሙ ከነአያት ይመዘገባል፡፡

Q.8 NAME OF INTERVIEWER

ጥ.8 የመረጃ ሰብሳቢው ሙሉ ስም

የመረጃ ሰብሳቢው ሙሉ ስሙ ከነአያት ይመዘገባል፡፡

## A.1 EA

**ሀ-1 - የቆጠራ ቦታ:-** በጥያቄው ሥር በተሰጡት ሦስት ክፍት ቦታዎች ላይ ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ መለያ ባለ 3 ድጂት ቁጥር (EA Code) ይመዘገባል::

## A.2- Household

**ሀ-2 - ቤተሰብ:-** በጥያቄው ሥር ባሉት ሁለት ክፍት ቦታዎች ላይ ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ የምርጫ ተራ ቁጥር የሚመዘገብበት ነው:: ለምሳሌ የተመረጠው ቤተሰብ በ8ኛው ደረጃ ተመርጦ ከሆነ በክፍት ቦታው ላይ 08 ይመዘገባል ማለት ነው::

## A.3- Interviewer

**ሀ-3 - መረጃ ሰብሳቢ:-** ለእያንዳንዱ መረጃ ሰብሳቢ ባለ ሦስት አሃዝ የመለያ ቁጥር በመ/ቤቱ ተዘጋጅቶ ይሰጠዋል:: ስለሆነም የተሰጠውን የመለያ ቁጥሩ በተሰጡት ክፍት ቦታዎች ላይ ማስፈር ያስፈልጋል::

## A.4- Date

**ሀ-4 - ቀን:-** በዚህ ስር ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ መረጃውን የተሰበሰበበት ቀን በመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍት ቦታዎች ላይ፣ መረጃው የተሰበሰበበት ወር በቀጣዩ ሁለት ክፍት ቦታዎች ላይ እና ዓመተ ምህረቱ ደግሞ በቀጣዮቹ ሁለት ክፍት ቦታዎች ላይ ይመዘገባሉ:: ከዚህ በታች የተመለከቱትን ምሳሌዎች ተመልከት:: የመጀመሪያው ምሳሌ ጥናቱ የሚካሄደው ሰኔ 20/1995 ቢሆን እንዴት እንደሚሞላ ሲሆን 2ኛው ደግሞ ጥናቱ የሚካሄደው ሐምሌ 09/1995 ቢሆን እንዴት እንደሚሞላ ለማመልከት ነው::

| | ቀን | | ወር | | ዓመት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሰኔ 20/1995 | 2 | 0 | 1 | 0 | 9 | 5 |
| ሐምሌ 09/1995 | 0 | 9 | 1 | 0 | 9 | 5 |

## A.5- Time

**ሀ-5 - ሰዓት:-** በዚህ ዓምድ ቃለ መጠይቁ የተጀመረበት ሰዓትና ደቂቃ ይመዘገባል:: መረጃ ሰብሳቢው ለቤተሰቡ ጥያቄዎች ከማቅረቡ በፊት የጀመረበትን ሰዓትንና ደቂቃውን

መመዝገብ አለበት። ከክፍት ቦታው ጎን የተሰጡት ሁለት አማራጮች (D,N) ለቀንና ማታ መለያ ሲሆኑ መጠይቁ ቀን ተሞልቶ ከሆነ "D" የሚለውን ማጥቆር ማታ ከሆነ ደግሞ "N" የሚለውን ማጥቆር ያስፈልጋል። ለዚህ ጥናት ቀን ማለት ከጠዋቱ 12:01-12:00 ሲሆን ማታ ደግሞ ከምሽቱ 12:01-በኋላ ያለውን ጊዜ ማለት ነው።

## A.6 - Respondent

**ሀ-6 - መልስ ሰጪ፡-** በዚህ ዓምድ በገጽ 2 ለተዘረዘሩት የቤተሰብ አባላት ከተሰጠው የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር መካከል የመልስ ሰጪው ቤተሰብ አባልን ተራ ቁጥር ይሞላል።

<u>ማስታዎሻ</u>

መልስ ሰጪው በተቻለ መጠን የቤተሰቡ ኃላፊ መሆን ይኖርበታል። ሆኖም መልስ ሰጪው ሌላ የቤተሰብ አባል ከሆነ በሀ-6 መመዝገብ ያለበት የመልስ ሰጭው ተራ ቁጥር ነው።

## A.7- SEQ.(Quest.No)

**ሀ-7 - መ.ቁ (የመጠይቅ ቁጥር):-** በዚህ ዓምድ የአንድ ቤተሰብ መረጃ በአንድ መጠይቅ ብቻ የሚጠናቀቅ ከሆነ 1 ተብሎ ይመዘገባል። ሁለተኛ መጠየቅ የሚያስፈልግ ከሆነ (ለምሳሌ ቤተሰቡ ከ10 አባላት በላይ ሲኖረው) ደግሞ ለሁለተኛው መጠይቅ 2 ተብሎ ይመዘገባል።

**Important:** Create a reference number by combining Identification Particulars Code and Household Number and questionniare numbers. Write this number NOW on the top of all pages.

**አብይ ማስታወሻ:-** የአካባቢ መለያ ቁጥር (ሀ-1)፣ ከተመረጠው ቤተሰቡ መለያ ቁጥር (ሀ-2) እና የመጠይቅ ቁጥሩን (ሀ-7) በማቀናጀት ጥናቱ የሚካሄድበት ቦታ ለመለየት የሚያስችል መለያ ቁጥርን በማዘጋጀት ቁጥሩ በእንያንዳንዱ የመጠይቁ ገጽ ራስጌ ባሉት ስድስት ሣጥኖች ላይ ማስፈር ያስፈልጋል።

ምሳሌ:- ጥናቱ የሚካሄድበት የቆጠራ ቦታ የሚገኘው ከዚህ በታች እንደተሰጠው ምሳሌ ቢሆን:-

| | ኮድ |
|---|---|
| ለቆጠራ ቦታው የተሰጠው መለያ ኮድ | 025 |
| የቤተሰብ ምርጫ ተራ ቁጥር | 08 |
| የመጠይቅ ቁጥሩ | 1 |

በእያንዳንዱ መጠይቅ ራስጌ ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ በሚከተለው ሁኔታ ይመዘገባል ማለት ነው።

የመጠይቁ መለያ ቁጥር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 0 | 2 | 5 | 0 | 8 | 1 |

Coments

**አስተያየት፡-** በዚህ ቦታ ላይ መረጃ ሰብሳቢውም ሆነ ተቆጣጣሪው ስለመረጃ አሰባሰቡና መረጃው ሲሰበሰብ ያገጣሙ ልዩ ሁኔታዎች እስመልከተው ያላቸውን ማንኛውንም አስተያየት ያሰፍራሉ።

## Section B - LIST OF HOUSEHOLD MEMBERS

## ክፍል ለ - የቤተሰብ አባላት ዝርዝርና አጠቃላይ መረጃ

በዚህ ክፍል ውስጥ መደበኛ የቤተሰብ አባላት ዝርዝር፣ ፆታ፣ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ከቤተሰቡ እንደተለዩ፣ ለቤተሰቡ ገቢ ያላቸው አስተዋፅኦ፣ ከቤተሰቡ ሃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና፣ ዕድሜና እንዲሁም ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ለሆናቸው የጋብቻ ሁኔታ መረጃ ይሰበሰባል።

MEMBER NUMBER

የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር ከ1 እስከ 10 ተራ ቁጥሮች የተሰጠ ሲሆን ከቤተሰብ ኃላፊው በመጀመር በቅደም ተከተል አባላቱን በሙሉ መመዝገብ ያስፈልጋል።

Write down the names of all persons who normally live and eat together in this household, starting with the head.

የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም፡- ለቤተሰብና ለቤተሰብ አባል የተሰጠውን ትርጉምና ጽንሰ ሃሳብ መሠረት በማድረግ የቤተሰብ አባላት ሙሉ ስም ተጠይቆ በእያንዳንዱ ዓምድ ወደ ቁልቁል ባሉት ክፍት ቦታዎች ላይ በሚከተለው ቅደም ተከተል ይመዘገባል፡-

-የቤተሰብ ሃላፊ፣
-የኃላፊው ሚስት/ባል፣
-ያላገቡ ልጆች በዕድሜ ቅደም ተከተል (ከትልቅ ወደ ትንሽ)፣
-ያገቡ ልጆችና እዚሁ ቤት አብረው የሚኖሩ የቤተሰባቸው አባላት፣
-ሌሎች ዘመዶች፣
-ዘመድ ያልሆኑ አባላት።

<u>ማሳሰቢያ፣</u>

1. በቅርብ የተወለዱ ህፃናት፣ የዕድሜ ባለፀጋ ሰዎች፣ የቤት ሠራተኞች ... ወዘተ እንዳይረሱ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

2. የቤተሰቡ አባላት ከ10 በላይ ከሆኑ ሁለት መጠይቆች መጠቀም ያስፈልጋል። ስለሆነም በ2ኛው መጠይቅ የሚሞላው የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር 11፣ 12፣ 13፣... ወዘተ እየተባለ ይመዘገብና በመጀመሪያው መጠይቅ ክፍል ሀ ያለውን መረጃ እንዳለ ወደ 2ኛው መጠይቅ ክፍል ሀ ይተላለፋል።

B - 1 Is [Name] male or female?

ለ - 1 የ(እገሌ/ሊ.ት) ፆታ ምንድን ነው?

ጾታ:- የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ፆታውን በመጠየቅ የሚጠቆር ሲሆን በእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ስም ስር በሚገኙ ክፀች ላይ ፆታው ወንድ (male) ከሆነ "M" ሴት (female) ከሆነች ደግሞ "F" የሚለው ክብ ይጠቆራል። በስም ብቻ ፆታው ምን እንደሆነ ማወቅ ስለማይቻል የእያንዳንዱን አባል ጾታ ጠይቆ ማጥቆር ያስፈልጋል። ምክንያቱም የአንዳንድ ሰዎች ስም ለሁለቱም ጾታዎች ሊያገለግል ስለሚችል (ምሳሌ. ዓድታን) የአባላቱን ስም ብቻ መሠረት በማድረግ ፆታቸውን በግምት ማጥቆር ስህተት ስለሚያስከትል ነው። በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ወንዶች በሴት ስም እንዲሁም ሴቶች በወንድ ስም ስለሚጠሩ ፆታ በሚጠቆርበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

B - 2 How many month has [Name] been away in the last 12 months?

ለ-2 (እገሌ/ሊ.ት) ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከቤተሰቡ ለምን ያህል ወራት ተለይቶ/ታ ነበር?

እያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል ባለፉት 12 ወራት ውስጥ ከቤተሰቡ መለየቱና አለመለየቱ፣ ከተለየ ደግሞ ለምን ያህል እንደተለየ ይጠየቃል። በሚገኘው መልስ መሠረትም በፍፁም ተለይቶ የማያውቅ ከሆነ "00" በእያንዳንዱ ተጠያቂ ቤተሰብ አባል አንፃር ባሉት ሣጥኖች ውስጥ የሚሞላ ሲሆን ተለይቶ የሚያውቅ ከሆነ ደግሞ በሳጥኖቹ ውስጥ ለምን ያህል ወራት ከቤተሰቡ እንደተለየ ተጠይቆ በቤተሰቡ አባል አንፃር በሙሉ ወር ይመዘገባል። ይህም ማለት አንድ ሰው 1 ወር ከ25 ቀን የተለየ ቢሆን 1 ወር ይመዘገብለታል ማለት ነው።

B - 3 Does [Name] contribute to household income?

ለ -3 (እገሌ/ሊ.ት) ለቤተሰቡ ገቢ አስተዋፅኦ ያደርጋል/ታደርጋለች?

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ለቤተሰቡ ገቢ አስተዋፅኦ የሚያበረክት ከሆነ አዎን (Yes) በሚለው ትይዩ ያለው ክብ የሚጠቆር ሲሆን የማያበረክት ከሆነ ደግሞ የለም (No) በሚለው ትዩዩ ያለ ክብ ይጠቆራል። የቤተሰብ ገቢ ሲባል በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተደረገውን አስተዋፅዖ የሚመለከት ነው።

B - 4 What is [Name] 's relationship to the head of household?

ለ-4 (እገሌ/ሊት) ከቤተሰቡ ሃላፊ ጋር ያለው/ያላት ዝምድና ምንድን ነው?

ከቤተሰብ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና:- ከላይ የቤተሰቡ አባላት ዝርዝር በሚመዘገብበት ጊዜ በመጀመሪያው ተራ ቁጥር የሚመዘገበው ሁልጊዜ የቤተሰቡ ኃላፊ ይሆናል:: ስለዚህ በB.4 በመጀመሪያው መስመር «ኃላፊ» /Head/ በሚለው ላይ ያለው ክብ ከጠቆረ በኋላ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያለው ዝምድና እየተጠየቀ ይጠቆራል ማለት ነው::

ለምሳሌ:- ከቤተሰቡ ኃላፊ ቀጥላ የተመዘገበችው የቤተሰቡ ኃላፊ ሚስት ከሆነች Spouse «ባለቤት» ከሚለው ትይዩ ይጠቆራል:: የቤተሰቡ ኃላፊ ከአንድ በላይ ሚስት ካለውና ሚስቶቹ የርሱ ቤተሰብ አባላት ከሆኑ ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸው ዝምድና ተመሳሳይ ይሆናል ማለት ነው::

የቤተሰቡ መደበኛ አባላት ከቤተሰቡ ኃላፊ ጋር ያላቸውን ዝምድና አጣርቶ በመጠየቅ ከእያንዳንዱ የዝምድና ዓይነት ጋር በማዛመድ መመደብ ያስፈልጋል:: ከዓምዱ ሥር የተዘረዘሩት የተለያዩ የዝምድና ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው::

| |
|---|
| 1= የቤተሰብ ኃላፊ (Head) |
| 2= የኃላፊ ሚስት ወይም ባል (Spouse) |
| 3= ልጅ (Child) |
| 4= የኃላፊ እናት ወይም አባት |
| 5= ሌላ ዘመድ (የባለቤት ልጅ፣ የባለቤት እናት አባት የሥጋና የጋብቻ ዝምድና፣ የማደጎና የክርስትና ልጅ ... ወዘተ) (Other relative) |
| 6= ዘመድ ያልሆነ (Non-relative) |

B -5 How old was [Name] at last birthday?

ለ -5 የ(እገሌ/ሊት) ዕድሜ ስንት ነው?

ዕድሜ:- እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ይህ ጥናት በሚካሄድበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ ዕድሜ ተጠይቆ በሙሉ ዓመት (በጨረሱት ዓመት) በተሰጠው ክፍት ቦታ ይመዘገባል:: ዕድሜ በሙሉ ዓመት ማለት ከሙሉ ዓመት በተጨማሪ ያሉትን ወሮችንና ቀኖችን በመተው ዓመቱን ብቻ በመውሰድ ዕድሜውን መመዝገብ ነው:: ለምሳሌ የአንድ ሰው ዕድሜ 15 ዓመት ከ11 ወር ከ29 ቀን ቢሆን

መመዝገብ ያለበት 15 ዓመት ብቻ ይሆናል እንጂ 16 ዓመት ሊሞላው አንድ ቀን ስለቀረው 16 ዓመት ተብሎ መሞላት የለበትም። የአንድ ህፃን ዕድሜ ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ «00» ይመዘገባል። እንዲሁም የአንድ ሰው ዕድሜ 97 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ «95» ብቻ ይመዘገባል።

ዕድሜያቸውን በትክክል የማያውቁ ወይም ዕድሜያቸውን ለመናገር ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች እንደሚያጋጥሙ ይገመታል። ስለዚህ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት በተቻለ መጠን ባለመሰልቸት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ከሚያስችሉት ዘዴዎች መካከል ቀጥሎ የተመለከቱትን ማጤን ይገባል።

ሀ. መልስ ሰጪው በተወለደበት ጊዜ/አካባቢ በብሄራዊ ደረጃ ወይም በሚኖርበት አካባቢ የተፈፀመ ታሪካዊ ድርጊት እንዳለና ቀጥሎም መልስ ሰጪው ድርጊቱ በተፈፀመ ጊዜ ዕድሜው ምን ያህል እንደነበረ ወይም ከድርጊቱ በኋላ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ እንደተወለደ በመጠየቅና ከዚያም ይህንን መረጃ መሠረት በማድረግ የግለሰቡን ዕድሜ ለመገመት መሞከር ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡- ግለሰቡ የ1966 አብዮት ከመፈንዳቱ 10 ዓመት ቀድሞ የተወለደ ከሆነ የግለሰቡ ዕድሜ በ1995 ዓ.ም. ከሞላ ጎደል (1995-1966)+10= 39 ዓመት ተብሎ ይመዘገባል። ስለዚህ የአንድን ግለሰብ የተወለደበት ዓመት ታሪካዊ ድርጊቶች ከተፈፀሙበት ዓመት ምሕረት ጋር በማነፃፀር ዕድሜውን ለመገመት ስለሚቻል ዋና ዋና ታሪካዊ ድርጊቶች የተፈፀሙበት ዓመት ምሕረት ዝርዝር ከዚህ ክፍል ቀጥሎ ይገኛል።

ለ. አንዳንድ የቤተሰብ አባላት ወይም በአካባቢው የሚኖሩ ግለሰቦች ዕድሜያቸውን በትክክል ሊያውቁና ሊናገሩ ይችሉ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ዕድሜያቸውን የማያውቁትን ሰዎች ዕድሜ ከነዚህ ዕድሜያቸውን ከሚያውቁ ሰዎች ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል።

ሐ. ከቤተሰቡ አባላት መካከል የአንዱ ዕድሜ በትክክል ከታወቀ፣ የሌሎችን ዕድሜ ለመገመት ይቻል ይሆናል። ለምሳሌ የአንድ ቤተሰብ የመጀመሪያው ልጅ ዕድሜው 13 ዓመት መሆኑ ከታወቀና የእናቱን ዕድሜ ለማወቅ ቢፈለግ የእናቱ ዕድሜ ቢያንስ 29 ዓመት ብሎ ለመገመት ይቻላል። ይህም ሊገኝ የሚቻለው እናቶች አብዛኛውን ጊዜ በ16 ዓመት የመጀመሪያውን ልጅ ይወልዳሉ ተብሎ ስለሚገመት የእናትየዋ ዕድሜ 16+13 = 29 ይሆናል። የሥጋ ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የአንዱን ዕድሜ ከሌላው በማነፃፀር ዕድሜያቸውን ለመገመት ይቻላል። ለምሳሌ አብዛኛውን ጊዜ እናቶች በየሁለት በየሁለት ዓመት ይወልዳሉ። የትንሹ ልጅ ዕድሜ 7 ዓመት መሆኑ

ከተረጋገጠ፣ የታላቁ ልጅ ዕድሜ 9 ዓመት ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም አንድ አባል ባገባበት ጊዜዕድሜው ስንት እንደነበረና በጋብቻ ስንት ዓመት እንደቆየ ከታወቀ ዕድሜውን ለመገመት ይቻላል። ዕድሜያቸው የገፉ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ዕድሜያቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል። የነኚህን ሰዎች ዕድሜ ከመጀመሪያው ልጃቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በማነፃፀር ለመገመት ይቻላል። ስለዚህ የአንዱ ቤተሰብ አባል ዕድሜ ከታወቀ ከሌላው አባል ጋር በማዛመድ በተቻለ መጠን ትክክለኛ የሆነውን ገምቶ መፃፍ ያስፈልጋል።

መ. አንዳንድ ሰዎች ዕድሜያቸውን በዜሮ ወይም በአምስት በሚያልቁ አሃዞች ለመናገር ይፈልጋሉ ወይም ይቀላቸዋል። ስለዚህ ዕድሜያቸውን መግለፅ የሚገባቸው ለመናገር በሚቀላቸው ወይም በሚፈልጉት ሳይሆን፣ ትክክለኛውን ዕድሜ ለማግኘት መሞከር ያስፈልጋል። አንዳንድ ሰዎች በእርግጥ ዕድሜያቸው 10፣ 15፣ 20፣ 25፣ ... ወዘተ ሊሆን ይችላል።

ሠ. ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት ያላለፉ ሕፃናት ልጆች የተወለዱበትን ጊዜ ወላጆቹ ሊያስታውሱት ስለሚችሉ የሕፃናትና ትናንሽ ልጆች ዕድሜ በሙሉ ዓመት በትክክል መፃፍ አለበት። አልፎ አልፎ የሕፃናትን ትክክለኛ ዕድሜ ለማግኘት ቀላል የማይሆንበት ሁኔታ ካጋጠመም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ትክክለኛውን ዕድሜ መመዝገብ ያስፈልጋል።

ከዚህ በላይ የተሰጡትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ የእያንዳንዱን የቤተሰብ አባል ዕድሜ ለማግኘት ትክክለኛ መልሶችን ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማቅረብና በማስላት በቂ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

# ዋና ዋና የታሪካዊ ድርጊቶች ዝርዝር

| ተራ ቁ. | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1995 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 1 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተወለዱበት | 1884 | 111 |
| 2 | ዝዋይ የተወረረበት(ከጂቡቲ እስከ አዲስ አበባ ያለው የባቡር መስመር የተዘረጋበት) | 1886 | 109 |
| 3 | የወላሞ ዘመቻ የተደረገበት | 1887 | 108 |
| 4 | ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ከኢጣሊያ ወታደር ጋር በኩዓቲት ላይ ጦርነት የገጠሙበት | 1887 | 108 |
| 5 | ራስ መንገሻ በኩዓቲትና በሰንዓፌ ላይ በኢጣልያን ድል የሆኑበት | 1887 | 108 |
| 6 | የዓድዋ ድል የተገኘበት | 1888 | 107 |
| 7 | ንጉሥ ተክለሃይማኖት ያረፉበት | 1893 | 102 |
| 8 | ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በጋራ ሙለታ ደጃዝማች ተብለው የተሾሙበት | 1897 | 98 |
| 9 | ልዑል ራስ መኮንን ያረፉበት | 1898 | 97 |
| 10 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲዳሞ የተሾሙበት | 1900 | 95 |
| 11 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐረርጌ የተሾሙበት | 1902 | 93 |
| 12 | አጼ ምኒልክ ያረፉበት (ልጅ ኢያሱ የነገሱበት) | 1906 | 89 |
| 13 | ራስ ሚካኤል በወሎ፣ በትግሬና በጎጃም የነገሱበት | 1907 | 88 |
| 14 | ንግሥት ዘውዲቱ የነገሱበት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ የሆኑበት | 1909 | 86 |
| 15 | የሰገሌ ጦርነት የተካሄደበት | 1909 | 86 |
| 16 | እቴጌ ጣይቱ ያረፉበት | 1910 | 85 |
| 17 | የኅዳር በሽታ የነበረበት | 1911 | 84 |
| 18 | ልጅ ኢያሱ የተያዙበት | 1913 | 82 |
| 19 | ኢትዮጵያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር አባል የሆነችበት | 1916 | 79 |

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1995 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 20 | የባሪያ ነጻነት ደንብ የወጣበት | 1916 | 79 |
| 21 | ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት የተቋቋመበት | 1917 | 78 |
| 22 | ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ያረፉበት | 1918 | 77 |
| 23 | አቡነ ማቴዎስ ያረፉበት | 1919 | 76 |
| 24 | ንግሥት ዘውዲቱ ያረፉበት | 1922 | 73 |
| 25 | ራስ ጉግሳ ወሌ በጎንደር የሞቱበት | 1922 | 73 |
| 26 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የነገሡበት | 1923 | 72 |
| 27 | የወልወል ግጭት የተደረገበት | 1927 | 68 |
| 28 | የማይጨው ጦርነት የተካሄደበት ኢጣሊያ ወደ ኢትዮጵያ የገባችበት | 1928 | 67 |
| 29 | የኢትዮጵያ ሰማዕታት ቀን | 1929 | 66 |
| 30 | በጂማ ገነቴ ላይ የአርበኞች ውጊያ የተደረገበት | 1930 | 65 |
| 31 | እንግሊዝ ኢጣልያን ከኢትዮጵያ ለማስወጣት የመጣበት | 1933 | 62 |
| 32 | ኢጣሊያን ድል የተመታችበት | 1933 | 62 |
| 33 | የመጀመሪያ ወያነ | 1935 | 60 |
| 34 | ለኢትዮጵያ ሰማዕታት ሀውልት የተሰራበት | 1937 | 58 |
| 35 | አቡነ ባስሊዎስ ሊቀ ጳጳስ የሆኑበት | 1943 | 52 |
| 36 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን የተዋሃደችበት | 1943 | 52 |
| 37 | የሸንቁጤ ረሀብ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የገባበት | 1950 | 45 |
| 38 | ዘመነ አንበጣ | 1951 | 44 |
| 39 | እነጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለመፈንቀል ሙከራ ያደረጉበት | 1953 | 42 |

| ተራ ቁጥር | ታሪካዊ ድርጊቶች | ድርጊቱ የተፈጸመበት ዓመተ ምሕረት | ድርጊቱ ከተፈጸመበት እስከ 1995 ዓ.ም. ያሉት ዓመታት ብዛት |
|---|---|---|---|
| 40 | ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሐደችበት | 1955 | 40 |
| 41 | የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት | 1955 | 40 |
| 42 | ኮሌራ በሽታ የገባበት | 1963 | 32 |
| 43 | የወሎ ድርቅ | 1965 | 30 |
| 44 | የኢትዮጵያ አብዮት የፈነዳበት | 1966 | 29 |
| 45 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን የወረዱበት | 1967 | 28 |
| 46 | የዕድገት በሕብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በዓል የታወጀበት | 1967 | 28 |
| 47 | የገጠርን መሬት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 28 |
| 48 | የከተማ ቦታ እና ትርፍ ቤት የመንግሥት ያደረገው አዋጅ የታወጀበት | 1967 | 28 |
| 49 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያረፉበት | 1967 | 28 |
| 50 | የራዛ ዘመቻ የታወጀበት | 1969 | 26 |
| 51 | የሱማሌ ዘመቻ | 1969 | 26 |
| 52 | ኢ.ሠ.ፓ.አ.ኮ. የተመሠረተበት | 1972 | 23 |
| 53 | የቀይ ኮከብ ዘመቻ | 1974 | 21 |
| 54 | ብሔራዊ ውትድርና የታወጀበት | 1975 | 20 |
| 55 | የመጀመሪያው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የተካሄደበት | 1976 | 19 |
| 56 | በትግራይና በወሎ ከፍተኛ ረሀብ የገባበት | 1977 | 18 |
| 57 | የኢ.ሠ.ፓ. ምሥረታና የ10ኛው አብዮት በዓል የተከበረበት | 1977 | 18 |
| 58 | የሰፈራ ፕሮግራም የታወጀበት | 1978 | 17 |
| 59 | የግንቦት 8 መፈንቅለ መንግሥት | 1981 | 14 |
| 60 | ኢሕአዴግ አዲስ አበባን የተቆጣጠረበት | 1983 | 12 |
| 61 | ሁለተኛው የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ የተካሄደበት | 1987 | 8 |
| 62 | የሽግግር መንግሥት ያከተመበት | 1987 | 8 |
| 63 | ኤርትራ ኢትዮጵያን የወረረችበት | 1990 | 5 |
| 64 | ዘመቻ ፀሐይ ግባት የተጠናቀቀበት | 1991 | 4 |
| 65 | የኤርትራ ወረራ ሙሉ በሙሉ የከሸፈበት | 1992 | 3 |

## B - 6 What is [Name] 's marital status?

## ለ -6 የ(እገሌ/ሊት) የጋብቻ ሁኔታ ምንድን ነው?

<u>የጋብቻ ሁኔታ</u>፡- ዕድሚያቸው 10 እና ከዚያም በላይ ለሆኑት የቤተሰብ አባላት በስማቸው እንጻር የጋብቻ ሁኔታ በመጠየቅ ከተሰጡት የጋብቻ ሁኔታዎች ዝርዝር ውስጥ ትክክለኛውን መርጦ ማጥቆር ያስፈልጋል፡፡

ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕጋዊ፣ በባሕላዊ ወይም በኃይማኖታዊ መንገድ የጋብቻ ሥነ ስርዓት ፈጽመው እንደ ባልና ሚስት አብረው ሲኖሩ ነው፡፡ የጋብቻውን ሁኔታ ለማመልከት ከዚህ በታች የተመለከቱት የጋብቻ ሁኔታዎች ተሰጥተዋል፡፡

Never married

**አግብተው የማያውቁ**

ፈጽሞ ያላገባች/ያላገባ ማለት እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ የትዳርን ነገር ያልሞከሩ ማለትም አግብታ የማታውቅ /አግብቶ የማያውቅ ማለት ነው፡፡

Married

**ባለትዳር**

ባለትዳር ማለት በጥናቱ ወቅት በጋብቻ ላይ ያለ/ያለች የቤተሰብ አባል ማለት ነው፡፡

Divorced

**የተፋቱ**

ከጥናቱ ቀን በፊት አግብታ ወይም አግብቶ የነበረች/የነበረ ነገር ግን ከጥናቱ ቀን በፊት በሕጋዊ/በባሕላዊ ወይም በኃይማኖታዊ መንገድ የተፋታች/የተፋታ የቤተሰብ አባል "የፈቱ የሚለው ይሞላላቸዋል፡፡

Separated

**የተለያዩ**

የተለያዩ የሚባለው ባልና ሚስት ባለመግባባት ምክንያት ጉዳያቸው በሽማግሌዎች በመታየት ላይ ያለ ወይም ፍርድ ቤት በቀጠሮ ላይ የሚገኙትን የሚመለከት ነው፡፡

Widowed

**የሞቱባቸው**

ባል የሞተባት ወይም ሚስት የሞተችበት ሆነው ከሞቱባቸው በኋላ እስከ ጥናቱ ቀን ድረስ ያላገቡ የቤተሰብ አባላትን ይመለከታል፡፡

B - 7 Is [Name] 's father alive?

ለ-7 የ(እገሌ/ሊት) አባት በሕይወት አሉ?

ዕድሚያቸው 17 ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑ የቤተሰብ አባላት አባታቸው በሕይወት መኖር አለመኖራቸው ተጠይቆ በሕይወት ካሉ በ"አዎን" አቅጣጫ ማጥቆር ከሌሉ ደግሞ በ"የለም" አቅጣጫ ማጥቆር ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪው የማያውቀው ከሆነ ግን "አይታወቅም" በሚለው አቅጣጫ ይጠቆራል::

B -8 Is [Name] 's father living in the household?

ለ-8 የ(እገሌ/ሊት) አባት ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ነው?

ዕድሜያቸው 17 ዓመትና በታች የሆኑ በጥያቄ ለ.7 ላይ አባታቸው በሕይወት አሉ ከተባሉ አባታቸው ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ መሆኑ አለመሆኑ ተጠይቆ በተገቢው ምርጫ መሠረት ይጠቆራል:: አባታቸው ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ከሆነ "አዎን" በሚለው አቅጣጫ ማጥቆር ከሌሉ ደግሞ "የለም" በሚለው አቅጣጫ ማጥቆር ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪው የማያውቀው ከሆነ ግን "አይታወቅም" በሚለው አቅጣጫ ይጠቆራል::

B - 9 Is [Name] 's mother alive?

ለ -9 የ(እገሌ/ሊት) እናት በሕይወት አሉ?

ዕድሜያቸው 17 ዓመትና በታች የሆኑ የቤተሰብ አባላት እናታቸው በሕይወት መኖር አለመኖራቸው ተጠይቆ እናታቸው በሕይወት ካለች "አዎን" አቅጣጫ ማጥቆር ከሌለች ደግሞ በ"የለም" አቅጣጫ ማጥቆር ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪው የማያውቀው ከሆነ ግን "አይታወቅም" በሚለው አቅጣጫ ይጠቆራል::

B - 10 Is [Name] 's mother living in the household?

ለ-10 የ(እገሌ/ሊት) እናት ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ ነው?

ዕድሜያቸው 17 ዓመትና በታች የሆኑ በጥያቄ B.9 ላይ እናታቸው በሕይወት አሉ ከተባለ እናታቸው ከቤተሰቡ ጋር እየኖሩ መሆኑ አለመሆኑ ተጠይቆ በተገቢው ምርጫ መሠረት ይጠቆራል:: እናታቸው ከቤተሰቡ ጋር በአንድነት እየኖሩ ከሆነ "አዎን" በሚለው አቅጣጫ ማጥቆር ከሌሉ ደግሞ "የለም" በሚለው አቅጣጫ ማጥቆር ያስፈልጋል:: መልስ ሰጪው የማያውቀው ከሆነ ግን "አይታወቅም" በሚለው አቅጣጫ ይጠቆራል::

## Section C - EDUCATION

## ክፍል ሐ - ትምህርት

በዚህ ቅጽ የሚሰበሰበው መረጃ ዕድሚያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት የትምህር ሁኔታን መመልከት ነው:: መረጃው የሚሰበሰበው በቅፅ B ላይ በተሰጠው የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር መሠረት ስለሆነ ከእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ተጠያቂውን የቤተሰብ አባል እና በቅፅ B የተሰጠውን የቤተሰብ አባላት ተራ ቁጥር በጥንቃቄ ማገናዘብ ያስፈልጋል::

### C.1 Can ( Name) Read and Write?

### ሐ.1 (እገሌ/ሊት) ማንበብና መፃፍ ይችላሉ?

በዚህ ዓምድ 5 ዓመትና ከዚያ በላይ ዕድሜ ያለው/ት የቤተሰቡ አባል ማንበብና መፃፍ መቻል አለመቻላቸው ተጠይቆ "አዎን" የሚል መልስ ከተገኘ "አዎን" በሚለው ትዩዩ ያለው ክብ ቦታ ሲጠቆር፣ አልችልም ካለ ደግሞ "የለም" በሚለው ትዩዩ ያለው ክብ ቦታ ይጠቆራል:: ነገር ግን ዕድሜው ከ5 ዓመት በታች ለሆነው የቤተሰብ አባል ጥያቄው ስለማይመለከተው ሳጥኖቹን ባዶ መተው አለባቸው:: አንድ ግለሰብ ማንበብና መፃፍ ይችላል የሚባለው ግለሰቡ በሚያውቀው ቋንቋ አንብቦ መረዳትና መፃፍ ሲችል ነው:: ሆኖም የራሳቸውን ስም ወይም ቁጥሮች ብቻ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ግለሰቦች የትምህርት ችሎታ እንዳላቸው አይቆጠሩም:: እንዲሁም ቀደም ብሎ በቃል የተጠኑ የሃይማኖት ነክ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮች ብቻ ማነብነብ የሚችሉ ነገር ግን መፃፍ የማይችሉ ከሆነ ማንበብና መፃፍ እንደሚችሉ አይቆጠሩም::

### C.2 Has (Name) Ever Attended School (Formal Education)?

### ሐ.2 (እገሌ/ሊት) መደበኛ ትምህርት ተከታትለው ያውቃሉ?

እድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ የቤተሰቡ አባል በሕይወቱ ውስጥ መደበኛ ትምህርት ተከታትሎ የሚያውቅ ከሆነ "አዎን" በሚለው ትዩዩ ያለው ሳጥን የሚጠቆር ሲሆን አልተከታተልኩም ካለ ደግሞ "የለም" በሚለው ትዩዩ ያለው ክብ ቦታ ይጠቆራል::

<u>ማሳሰቢያ:-</u> በዚህ ጥያቄ የቤተሰቡ አባል በሕይወቱ መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ተመዝግቦ የማያውቅ ከሆነ በዚህ ክፍል ያሉ ሌሎች ጥያቄዎች ስለማይመለከቱት ወደ ሚቀጥለው ሰው ማለፍ ያስፈልጋል::

C.3 What is the highest grade (Name) completed?

## ሐ.3 (እገሌ/ሊት) የፈፀሙት ከፍተኛ ክፍል ስንት ነው?

ይህ ጥያቄ የሚመለከተው ዕድሜያቸው 5 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆናቸውን ሆኖ በመደበኛ ት/ቤት አሁን በመማር ላይ ያሉትን፣ በየትኛውም ዘመን መደበኛ ትምህርት ያቋረጡትን፣ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁትን/ያቆሙትን ነው።

ትምህርት ሲማሩ ቆይተው ያቋረጡ/ያቆሙ ወይም ትምህርታቸውን ያጠናቀቁን የቤተሰቡ አባላት ያጠናቀቁት ከፍተኛ ክፍል በመጠየቅ ይሞላላቸዋል። አሁን በመማር ላይ ላሉት ደግሞ ከጥናቱ ዓመት በፊት ያጠናቀቁት ከፍተኛ ክፍል ተጠይቆ ተገቢው ኮድ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ይሞላላቸዋል።

ለጥያቄ ሐ.3, ሐ.5, እና ሐ.7 የሚያስፈልግ የትምህርት ደረጃና ኮድ

| ኮድ | በፊደል | የክፍል መረጃ |
|---|---|---|
| 00 | መዋለ ህፃናት | የመዋለ ህፃናት (ኬጂ) ዜሮ ክፍል (ፕሪፓራቶሪ) ነርሰር በመባል የሚታወቁትን ትምህርት የጨረሱ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ። እንደዚሁም በትምህርት ዘመኑ (ጥናቱ ሲካሄድ) አንደኛ ክፍል በመከታተል ላይ የሚገኙትን ይጨምራል። |
| 01 | አንደኛ | የአንደኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 02 | ሁለተኛ | የሁለተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 03 | ሦስተኛ | የሦስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 04 | አራተኛ | የአራተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 05 | አምስተኛ | የአምስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 06 | ስድስተኛ | የየስድስተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 07 | ሰባተኛ | የሰባተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 08 | ስምንተኛ | የስምንተኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 09 | ዘጠነኛ | የዘጠነኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |
| 10 | አስረኛ | የአስረኛ ክፍል ትምህርት ላጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| 11 | አስራ አንደኛ | የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ:: |
| 12 | አስራ ሁለተኛ | የአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት ሳጠናቀቁና ማንበብና መፃፍ የሚችሉ ሁሉ:: |
| 13 | ሰርተፊኬት | ከ12ኛ ክፍል በላይ በመደበኛ ትምህርት ቤቶች ወይም ከፍተኛ ትምህርት መስጫ፣ ከታወቁ ተቋሞች (ኮሌጅ) ዩኒቨርሲቲዎች ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ለማግኘት ባልታቀደ ፕሮግራም የአንደኛ ዓመት እና ከዚያ በላይ ትምህርት ለፈፀሙ ሁሉ ፕሮግራሙን አጠናቀው ሰርተፊኬት ለተቀበሉ ሁሉ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ:: |
| 14 | ኮሌጅ (ዩኒቨርሲቲ) | ከአስራ ሁለተኛ ክፍል ትምህርት በላይ በከፍተኛ ትምህርት መስጫ ከታወቁ ተቋማት ወይም ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ወይም ከተመሳሳይ ትምህርት መስጫ ተቋም ዲፕሎማ ወይም ከዚያ በላይ ለማግኘት በታቀደ የትምህርት ፕሮግራም ቢያንስ የአንድ ዓመት ትምህርት ያጠናቀቁ ሁሉ ኮድ 14 ይሰጣቸዋል:: |

ማሳሰቢያ፡ መደበኛ ያለሆነ ትምህርት የተከታተሉት ማንበብና መፃፍ መቻል አለመቻላቸው ብቻ ተጠይቶ ሌሎቹ ጥያቄች በሙሉ እንደማይመለከታቸው ማስታዋል ያስፈልጋል:: መደበኛ ያልሆነ ትምህርት የሚባሉት:-

1ኛ. የቄስ፣ የቁርዓን ትምህርት የመሳሰሉት፣
2ኛ. መሠረተ ትምህርት የተከታተሉ እና
3ኛ. በራሳቸው ጥረት ወይም በሌሎች ድጋፍ ማንበብና መፃፍ የቻሉ::

በአጠቃላይ ትምህርታቸው ወደ መደበኛ የትምህርት ደረጃ አመዳደብ ሊተርጎም የማይቻል በሙሉ መደበኛ ያለሆኑ ተብለው ይተረጎማሉ::

**C.4 Did (Name) registor to attend school last year?**

ሐ.4 ባለፈው የትምህርት ዘመን (እገሌ/ሊት) ትምህርት ለመከታተል ተመዝግበው ነበር?

ተመዝግበው ከነበሩ በየስማቸው አንፃር "አዎን" በሚለው የተከበበው የሚጠቆር ሲሆን ካልተመዘገቡ ደግሞ "የለም" በሚለው የተከበበው ማጥቆር ያስፈልጋል::

C.5 What is the grade (NAME) registored for last year?

ሐ.5 (እገሌ/ሊት) ባለፈው የትምህርት ዘመን ስንተኛ ክፍል ተመዝግበው ነበር?

በጥያቄ ሐ.4 ላይ የቤተሰብ አባል ባለፈው የትምህርት ዘመን ትምህርት ለመከታተል ተመዝግቦ/ባ ከነበረ ስንተኛ ክፍል እንደሆኑ ተጠይቆ ኮዱ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ይመዘገባል::

**C.6 Is (Name) Currently registered to attend school?**

ሐ.6 በያዝነው የትምህርት ዘመን (እገሌ/ሊት) ትምህርት ለመከታተል ተመዝግቧል/ባለች?

የቤተሰቡ አባል በትምህርት ዘመኑ ተመዝግበው ከሆነ በስማቸው አንፃር "አዎን" ከሚለው አቅጣጫ ማጥቆር የሚያስፈልግ ሲሆን ካልተመዘገቡ ደግሞ "የለም" በሚለው አቅጣጫ ይጠቆራል:: ስለሆነም በያዝነው ዓመት ላልተመዘገቡ ("የለም" ለተጠቆረላቸው) የቤተሰቡ አባላት የሚመለከታቸው ቀጣይ ጥያቄ በሐ.10 ያለው ብቻ በመሆኑ ከሐ.7 ሐ.9 ያለው ይዘለላል::

C.7 What is the currernt grade (Name) is registered to attend?

ሐ.7 (እገሌ/ሊት) በያዝነው የትምህርት ዘመን ተመዝግበው ከነበሩ የተመዘገቡበት ክፍል ስንት ነው?

ይህ ጥያቄ ከጥያቄ ሐ.6 ጋር የተያያዘ ነው:: ጥናቱ በሚካሄድበት ዓመት ባለው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ለመከታተል የተመዝግበው የቤተሰቡ አባላት (በጥያቄ ሐ.6 «አዎን» ለመለሱ) ስንተኛ ክፍል እንደተመዘገቡ ተጠይቀው ለዚህ በተዘጋጀው ቦታ ተገቢው ኮድ ይሞላ:: በአምዱ የሚሞላው የትምህርት መረጃ ኮድም ከላይ ለእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ በተሰጠው ኮድ መሠረት ነው:: በጥያቄ ሐ.6 «የለም» ለመለሱት ግን ይህ ጥያቄ ይዘለላል::

C.8 Who runs the school (Name) is attending ?

ሐ.8 (እገሌ/ሊት) የሚማርበት/የምትማርበት ትምህርት ቤት የሚያስተዳድረው ማን ነው?

ጥናቱ በሚካሄድበት ዓመት ባለው የትምህርት ዘመን መደበኛ ትምህርት ለመከታተል ተመዝግበናል ያሉ የቤተሰቡ አባላት በጥያቄ ሐ.6 ላይ «አዎን» ለመለሱ የሚማሩበት ትምህርት ቤት የማን እንደሆነ በመጠየቅ ከተሰጡት 5 አማራጮች በመምረጥ ይጠቆራል:: መደበኛ የትምህርት ቤቶች ዓይነት ለመለየት የሚከተሉትን አጭር መግለጫዎች ይጠቀሙ::

1. Government

1. የመንግሥት

የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚባሉት በትምህርት ሚኒስቴር፣ በግብርና ሚኒስቴር፣ በትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፣ በማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በመከላከያ ሚኒስቴር እንዲሁም እነዚህን በመሳሰሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ቁጥጥር ስር የሚተዳደሩ መደበኛ ትምህርት ቤቶችን፣ ዩኒቨርሲቲዎችንና ኮሌጆችን ያጠቃልላል:: በተጨማሪም የክልል መንግስታት ስር የሚተዳደሩትንም የመንግስት ት/ቤቶች የሚያጠቃልል መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

2. Mission/NGO

2. የሚሲዮን/ግብረ-ሰናይ ድርጅት

እነዚህ የመንግስት እርዳታ በማግኘትም ሆነ ባለማግኘት የቤተ ክህነት ወይም በሃይማኖታዊ ሚሲዮን ድርጅት ወይም ሙስሊም ድርጅት መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው:: መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (NGO'S) የሚደገፉ እና የሚተዳደሩ መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች በዚህ ይካተታሉ::

3. Private

3. የግል

የግል ትምህርት ቤቶች የሚባሉት ከሃይማኖት ነክ ድርጅቶች፣ ከግብረ ሰናይ ድርጅቶችና ዕርዳታ ድርጅቶች ውጪ ሙሉ በሙሉ በሌላ መንግስታዊ ባልሆኑ ወይም በሼር ለትርፍ ተብለው የተቋቋሙ መደበኛ ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው::

4. Community

4. የሕዝብ

የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የሚባሉት የመንግስት እርዳታ በማግኘትም ሆነ ባለማግኘት በውስጣቸው የሚማሩ ተማሪዎች በሚያደርጉት ክፍያና በየአካባቢያቸው በሚገኘው ተገልጋይ ሕዝብ በሙሉ ቁጥጥር በመተዳደር መደበኛ ትምህርት የሚሰጥባቸው ናቸው::

5. Other

5. ሌላ

በልዩ ልዩ የውጪ ሃገር መንግስታት እየተረዱ ወይም እያስረዱ ለዜጎቻቸው ልጆች መደበኛ ትምህርት የሚሰጥ የውጪ ኮሚኒቲ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ሌሎች ከላይ ከተራ ቁጥር ከ1-4 ውጪ ያሉት በሙሉ በዚህ ክፍል ይመደባሉ::

## C.9 Did (Name) have any problems with the school?

## ሐ.9 (እገሌ/ሊት) የሚማሩበት ት/ቤት ውስጥ ምን ዓይነት ችግር አለ?

ይህ ጥያቄ ተማሪው በመማር ማስተማር ሂደት ያጋጠሙ ችግር ካለ ለመዳሰስ የሚያስችል ነው:: ጥያቄው የሚመለከተው በያዝነው የትምህርት ዘመን በመማር ላይ ያሉትን የቤተሰብ አባላት ብቻ የሚመለከት ሲሆን አጠያየቁ በሚከተሉት ሁኔታ መከናወን ይኖርበታል::

መረጃ ሰብሳቢው ከዚህ በታች የተሰጡትን ምርጫዎች በመጠቆም ስለእያንዳንዱ በተናጠል በመጠየቅ ችግሮቹ ካሉ ችግሮቹን ከተዘረዘሩ አማራጮች መካከል በመምረጥ ማጥቆር ያስፈልጋል::

ችግሮቹም:-

Lack of books/Supplies

የመፃህፍት/የትምህርት መሳሪያ እጦት/እጥረት

Poor teaching

ደካማ የማስተማር ዘዴ

Lack of teachers

የመምህራን እጥረት

Facilities in bad condition

የአገልግሎት አሰጣጥ ችግር (የላብራቶሪ፣ የቤተ መፃህፍት፣ የመማሪያ ክፍሎች አለመሟላት፣ የክፍል መጨናነቅ ... ወዘተ)

Other Problem

ሌሎች ችግሮች

ከአንድ በላይ ችግሮች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ ለመልስ ሰጪው እያንዳንዱን በመጥቀስ መጠየቅ እንደሚያስፈልግ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ይሁን እንጂ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ምንም ዓይነት ችግር ላላጋጠመው ተማሪ በመጠይቁ ካሉት ምርጫዎች መካከል በመጀመሪያ ደረጃ የተመዘገበው "No" Problem/satisfied" የሚለው ይጠቆርለታል::

## C.10 Why is (Name) not currently in school?

## ሐ.10 በአሁን ጊዜ (እገሌ/ሊት) የማይማሩት ለምንድን ነው?

ይህ ጥያቄ የሚቀርበው በጥናቱ ዘመን በትምህርት ገበታ ላይ ላልሆኑ የቤተሰብ አባላት ሲሆን የሚሞላውም አባላቱ ለምን እንደማይማሩ በመጠየቅ የሚሰጡትን መልስ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ጋር በማገናዘብና በመለየት በትክክለኛ ቦታቸው ላይ በማጥቆር ነው:: ምክንያቶቹም ከዚህ በታች ተሰጥቷል::

To old/complete school

በዕድሜ ስለገፉ/ትምህርታቸውን ስላጠናቀቁ

Too far away

ት/ቤቱ ስለራቀባቸው

Too expensive

ውድ ስለሆነ

Is working (home or job)

በስራ ምክንያት (የቤት ውስጥ ስራ ወይም ከቤት ውጭ ስራ)፣ሥራ በመፈለግ

Father/mother ill/deceased

አባት/እናት ስለታመሙ/ስለሞቱ

Useless/uninteresting

በትምህርቱ አለመሳብ/የትምህርት ፍላጎት ማጣት

Illness

በህመም

Pregnancy

በእርግዝና/ወሊድ ምክንያት

Failed exam

በፈተና ስለወደቀ

Got married

በጋብቻ ምክንያት

Other

ሌላ

## Section D -HEALTH

## ክፍል መ -ጤና

በዚህ ቅጽ የሚሰበሰበው መረጃ ለሁሉም የቤተሰብ አባላት ነው:: መረጃው የሚሰበሰበው ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በተሰጠው የቤተሰቡ አባላት ተራ ቁጥር መሠረት በመሆኑ ጥያቄው የሚመለከተው የቤተሰብ አባል በመጠይቁ ገጽ-2 ላይ ከተሰጠውን ተራ ቁጥር ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል::

**D.1 Did (Name) have a live birth in the last 12 months?**

*መ.1 ባለፉት 12 ወራት ውስጥ (እገሊት) ህይወት ያለው ልጅ ወልዳ ነበር?*

እድሚያቸው 15 ዓመትና በላይ የሆናቸው ሴቶች ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በሕይወት የወለዱት/ዳት ህፃን መኖር አለመኖሩን አጣርቶ በመጠየቅ አዎ የሚል መልስ ከተገኘ "Y" ተብሎ የተከበበውን ማጥቆር ካልወለዱ ደግሞ "N" የሚለውን ማጥቆር ያስፈልጋል:: መረጃው ወንዶችን በሙሉና ዕድሚያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑትን ስለማይመለከት በቀጥታ ወደ ጥያቄ ተራ ቁጥር መ.3 ማለፍ ያስፈልጋል:: እንዲሁም በጥያቄ ቁጥር መ.1 ላይ የተገኘው መልስ "አልወለድኩም" የሚል ከሆነ ወደ ጥያቄ ቁጥር መ.3 ይታለፋል::

<u>ማስታወሻ፡-</u> ሕይወት ያለው ልጅ ተወለዷል የሚባለው ካረገዘች ሴት ማህፀን ህፃኑ እንደወጣ ወዲያውኑ ሕይወት ያለው መሆኑ ከታወቀ ነው:: ሕይወት ያለው መሆኑ የሚታወቀው ሕፃኑ ከእናቱ ማሕፀን እንደወጣ ወዲያውኑ ካለቀሰ፣ ከተነፈሰ፣ ልቡና እትብቱ ላይ ትርታ ከታየ ወይም ከተንቀሳቀሰ ነው:: ከላይ ከተሰጠቀሱት ምልክቶች ቢያንስ አንዱ ካልታየ ሕፃኑ በሕይወት እንደተወለደ አይቆጠርም::

**D.2 Did (Name) receive pre-natal care during the pregnancy?**

*መ.2 በእርግዝና ወቅት (እገሊት) የቅድመ-ወሊድ የጤና ምርመራ አድርገው ነበርን?*

በዚህ ጥያቄ ላይ (በጥያቄ መ.1 ላይ "አዎ" ለመለሱ) ሴቶች በእርግዝናቸው ወቅት ለህፃኑና ለእናትዬው ጤንነት አስፈላጊ የሆኑ የቅድመ-ወሊድ የጤና ምርመራዎች አካሂደው መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው የሚጠየቅበት ነው:: የቅድመ-ወሊድ ምርመራ ሲባል በእርግዝና ወቅት የሚከሰቱ የጤና ችግሮችን ለማወቅ የሚረዳ የደም፣ የሽንት፣ የደም ግፊት እና የመሳሰሉ የጤና ምርመራዎችን አድርገው ከነበረ እንዲሁም ለሕፃኑ ጤንነት ሲባል በእርግዝና ወቅት የመንጋጋ ቆልፍ (Titanus Toxoid TT) ክትባት የወሰዱትን የሚያጠቃልል የጤና ምርመራ ነው:: ነገር ግን በወሊድ ወቅት የተከናወነ የማዋለድ ተግባር እንደ ቅድመ-ወሊድ ምርመራ እንደማይቆጠር መገንዘብ ያስፈልጋል::

**D.3 was (Name) physically or mentally handicapped or disabled?**

**መ.3 (እ ገሌ/ሊ ት) የአካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ነውን?**

አንድ ሰው የአካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ነው የሚባለው በአካል ጉዳተኛነቱ ወይም በአዕምሮ ህመምተኛነቱ ምክንያት ሥራ /ለመስራት/ ወይም ትምህርት ለመከታተል አለመቻሉ ሲረጋገጥ ብቻ ነው:: ይሁን እንጂ የአካል ጉዳቱ ወይም የአዕምሮ በሽታው መደበኛ ተግባር ለማከናወን ወይም ትምህርቱን ለመከታተል ጉልህ ተፅእኖ ካላሳደረበት እንደ አካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ሆኖ መቆጠር የለበትም:: በዚህም መሠረት አጣርቶ በመጠየቅ የቤተሰቡ አባል የአካል ጉዳተኛ ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ መሆኑ ከተረጋገጠ "Y" የተሞላበት ክብ የሚጠቆር ሲሆን፣ ካልሆነ ደግሞ "N" የተሞላበት ክብ ይጠቆራል::

ማሳሰቢያ:- ይህ ጥያቄ ለሁሉም የቤተሰብ አባል እንደሚጠየቅ መዘንጋት የለበትም::

**D.4 Is (Name) sick or injured in the last 2 months?**

**መ.4 ባለፉት 2 ወራት ውስጥ (እ ገሌ/ሊ ት) ህመም ወይም አደጋ አጋጥምዎችው ነበር?**

ይህ ጥያቄ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚቀርብ ነው:: የቤተሰቡ አባላት ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ የጤና መታወክ (ሕክምና ሊወስዱም ላይወስዱም ይችላሉ) ወይም አደጋ አጋጥሟቸው ከነበረ በዓምዱ ስር "Y" ያለበት ክብ የሚጠቆር ሲሆን ምንም የጤና ችግር ካላጋጠመው ደግሞ "N" ያለበት ክብ ይጠቆራል::

ሕመም ማለት የአካል ወይም የአዕምሮ ደህንነት መጓደል ማለት ሲሆን ማንኛውም የቤተሰቡ አባል ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ለአጭር ጊዜ/ቢያንስ ለአንድ ሰዓት/ታሞ ከነበረ የጤና ችግር እንዳጋጠመው ይወሰዳል::

አንድ ሰው በአደጋ ምክንያት የጤና ችግር አጋጥሞታል የሚባለው በጉዳቱ ምክንያት ቢያንስ ለአንድ ሙሉ ቀን የዘወትር ተግባሩን ለማከናወን ካልቻለ፣ አደጋው ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ሕክምና ያደረገ፣ ወይም በአደጋው ምክንያት ሕክምና አስፈልጎት ያጣን ግለሰብ ያጠቃልላል::

ማስታወሻ:-

1. ባለፉት ሁለት ወራት ሲባል መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡን ከጎበኘበት ቀን በፊት ካለው ቀን ጀምሮ ወደ ኋላ ሁለት ወራት በመቁጠር ያለው ጊዜ ነው::

ለምሳሌ:- መረጃ ሰብሳቢው ቤተሰቡን የጎበኘው ጥር 10 ቀን ቢሆን ባለፉት ሁለት ወራት የሚመለከተው ጊዜ ከጥር 9 ቀን እስከ ህዳር 10 ቀን ይሆናል ማለት ነው።

የቤተሰቡ አባል የጤና ችግር ካላጋጠመኝም ካ ጥያቄ መ.5 እና መ.6 ስለማይመለከተው በቀጥታ ወደ ጥያቄ ቁጥር መ.7 ይታለፋል።

**D.5 What sort of sickness/injury did (Name) suffer?**

መ.5 የ(እገሌ/ሊት) ህመም ወይም አደጋ ምን ነበር?

በጥያቄ ቁጥር መ.4 ላይ ህመም ወይም አደጋ አጋጥሞናል ላሉ የቤተሰቡ አባላት የህመማቸውን ወይም የአደጋውን ዓይነት በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የበሽታ ዓይነቶች ጋር በማዛመድ ትክክለኛው መልስ ይጠቆራል። ለግለሰቡ (የቤተሰቡ አባል) ባለፉት 2 ወራት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ የህመም ዓይነት ሊያጋጥመው ስለሚችል በጥንቃቄ ጠይቆ ትክክለኛውን መልስ/መልሶች ማጥቆር ያስፈልጋል።

ማሳሰቢያ:- አንድ አባል ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ ከአንድ በላይ ህመም አጋጥሞት ከአንድ በላይ መልስ ሊጠቆር እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

| የህመም ዓይነቶች ዝርዝር | |
|---|---|
| Malaria | ወባ |
| Diarrhea | ተቅማጥ |
| Injury | አደጋ |
| Dental | የጥርስ ሕመም |
| Skin condition | የቆዳ በሽታ |
| Eye | የአይን ህመም |
| Ear, nose, or throat (ENT) | የጆሮ፣ የአፍንጫ ወይም የጉሮሮ ህመም /ከአንገት በላይ በሽታ/ |
| Other | ሌላ |

**D.6 How many days of work/school did (Name) miss due to illness/injury during the last 2 months?**

መ.6 ባለፉት 2 ወራት (እገሌ/ሊት) ለምን ያክል ቀን በህመም/አደጋ ምክንያት ከመደበኛ ተግባርዎ (ከስራ፣ ከትምህርት፣ ከጨዋታ ... ወዘተ ተለዩ?

በጥያቄ ተራ ቁጥር መ.4 ታሞ/ጉዳት ደርሶበት እንደነበረ ለገለፀው ለያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በህመሙ/በደረሰበት አደጋ ምክንያት ለምን ያህል ቀን/ቀናት ከመደበኛ ሥራው እንደተስተጓጎለ ወይም ትምህርቱን እንዳቋረጠ ተጠይቆ ትክክለኛው መልስ በቤተሰብ አባል ተራ ቁጥሩ አንፃር ይመዘገብለታል:: በዚህም መሠረት ምንም እንኳን ቢታመምም ከመደበኛ ተግባሩ (ሥራ/ትምህርት) ካልተስተጓጎለ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ "00" ይሞላለታል:: ሆኖም አደጋ አጋጥሞኝ ነበር ላሉ የቤተሰብ አባላት በዚህ ጥያቄ ቢያንስ ቢያንስ ለ1 ቀን መደበኛ ሥራቸውን/ትምህርታቸውን ያቋረጡ መሆን አለባቸው::

**D.7 Did (Name) consult a health provider or traditional healer for any reason in the last 2 months?**

**መ.7 ባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ (እገሌ/ሊት) ወደ ጤና ተቋማት ወይም በህላዊ ሐኪም ሄደው ነበርን?**

የቤተሰቡ አባላት የጤና ችግር አጋጥሟቸው ወይም ሳያጋጥማቸው የጤናቸው ሁኔታ ለመከታተል ሲሉ ወደ ዘመናዊ ህክምና መስጫ ወይም ወደ ባህላዊ የህክምና በመሄድ ምርመራ ካደረጉ "Y" የሚለው ክብ የሚጠቆርላቸው ሲሆን ምርመራ ያላደረጉ ከሆነ ግን "N" በሚለው አንፃር ያለው ክብ ይጠቆራል:: አንድ ሰው የሕክምና ክትትል (ምርመራ) አድርጓል የሚባለው በዘመናዊ የሕክምና ማዕከሎች ማለትም እንደ ሆስፒታል፣ ጤና ጣቢያ፣ ክሊኒክ ከመሳሰሉት እንዲሁም ዘመናዊ የሕክምና መገልገያዎችን በመጠቀም በቤታቸውም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ሕክምና ከሚያደርጉ ግለሰቦች፣ ከባሕላዊ አካሚዎችና በመሳሰሉት ምርመራ ከተደረገለት ወይም የምክር አገልግሎት ካገኘ ነው:: ነገር ግን የጥንቆላ ተግባር ከሚያከናውኑ፣ ከበሮ ከሚመቱ፣ ጨሌ ከሚጥሉት ሰይጣን እናወጣለን ከሚሉ፣ መንፈሳዊ ሰበካ ከሚያደረጉ፣ የጠበልና የእምነት አገልግሎት ከሚሰጡና ከመሳሰሉት የሚገኘው አገልግሎት <u>በዚህ ጥናት</u> እንደ ሕክምና አገልግሎት አይቆጠርም::

**D.8 What kind of health provider did (Name) See?**

**መ.8 (እገሌ/ሊት) የሄዱበት የህክምና አገልግሎት ሰጪ የትኛው ነው?**

የቤተሰቡ አባል ባለፉት 2 ወራት የሕክምና አገልግሎት ያገኙበትን ተቋም ከተዘረዘሩት አስር አማራጮች ውስጥ በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በይበልጥ የጎበኙትን/አብዛኛውን ሕክምና ያደረገበትን አንድ ተቋም በመለየት ይጠቆራል:: ለምሳሌ:- የሕክምና አገልግሎት የተገኘበት/የጎበኘው የሕክምና ተቋም በሚሲዮን ቢሆን "Mission/NGO" በሚለው አንፃር ያለውን ክብ ይጠቆራል::

| የሕክምና ተቋማት | | ኮድ |
|---|---|---|
| Traditional healer | -የባህል አካሚ | 0 |
| Hospital (Governmental) | - ሆስፒታል (የመንግስት) | 1 |
| Health Center (Governmental) | - ጤና ጣቢያ (የመንግስት) | 2 |
| Clinic (governmental) | - ክሊኒክ (የመንግስት) | 3 |
| Health Post (Governmental) | - የጤና ኬላ (የመንግስት) | 4 |
| Private Clinic/Hospital | - የግል ክሊኒክ/ ሆስፒታል | 5 |
| Mission/NGo | - የሚስዮን /ግብረ-ሰናይ | 6 |
| Private Health Personnel | - ግለሰብ (የጤና ባለሙያ) | 7 |
| Pharmacy | - ፋርማሲ | 8 |
| Other | - ሌላ | 9 |

<u>ማሳሰቢያ</u>:- የሕክምና ተቋማትን ለመለየት የሚከተለውን ማብራሪያ መከተል ያስፈልጋል:-

ሀ. <u>የግል ሆስፒታል</u>:- በግል/በማህበር/ በሽርክና የሚገኙ/ የመንግስት ያልሆኑ ሆስፒታሎች ናቸው:: ለትርፍ የተቋቋሙ የሐይማኖት ድርጅቶች፣ ሆስፒታሎችና ሌሎች ሆስፒታሎች በዚህ ይመደባሉ:: በጤና ጥበቃ መስፈርት መሠረት የእነዚህ ሆስፒታሎች ደረጃ መለስተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛና ልዩ ሆስፒታል በመባል ይታወቃል::

ለ. <u>የግል ክሊኒክ</u>:- በግል/በማህበር/ በሽርክና የሚገኙ/ የመንግስት ያልሆኑ ክሊኒኮች ናቸው:: ለትርፍ የተቋቋሙ የሐይማኖት ድርጅቶች ክሊኒኮችና ሌሎች መሰል ክሊኒኮች በዚህ ይመደባሉ:: የነዚህም ክሊኒኮች ደረጃ መለስተኛ፣ መካከለኛ፣ ከፍተኛና ልዩ ክሊኒክ በመባል ይታወቃል::

ሐ. <u>የሚስዮን</u>:- ከመንግስት ይዞታ ውጭ የሆኑና ትርፍ ለማግኘት ያልተቋቋሙ የሐይማኖት ድርጅቶች እና ሌሎች የሕክምና ተቋማትን የሚያጠቃልል ነው:: እነዚህ ተቋማት በሆስፒታል፣ በክሊኒክ፣ በጤና ጣቢያና በመሳሰሉት ደረጃዎች የሚገኙ ሊሆኑ ይችላሉ::

<u>ምሳሌ</u>:- የካቶሊክ ሚሲዮን፣ የመካነ ኢየሱስ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ የእስልምና ሐይማኖት ድርጅቶች ...ወዘተ. የተቋቋሙ የሕክምና ማዕከላት በዚህ ይካተታሉ::

መ. <u>ግለሰብ</u>:- (የጤና ባለሙያ) ምንም ዓይነት የጤና ተቋም ሳይኖራቸው በግል በቤታቸው ወይንም በጤና ተቋም ባልሆነ ሌላ ቦታ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ በዚህ ይመደባል::

ሠ. <u>ፋርማሲ፡-</u> ምንም እንኳን ፋርማሲ በሐኪም የታዘዘ መድኃኒት በመሸጥ ተግባር የተሰማራ ድርጅት ቢሆንም የሕክምና አገልግሎት ጭምር እንደሚሰጡ ይታወቃል። ስለሆነም ሐኪም ሳያማክሩ በቀጥታ የፋርማሲ ሠራተኞችን በማማከር የሕክምና አገልግሎት ያገኙ የቤተሰብ አባላት በዚህ ይካተታሉ።

ረ. <u>የባሕል አካሚ፡-</u> ባሕላዊ መድኃኒቶችን (ቅጠላ ቅጠሎች፣ ሥራ ሥሮች ...ወዘተ.) ተጠቅመው የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው።

ሰ. <u>ሌላ፡-</u> ከላይ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ተራ ቁጥር ከተጠቀሱት የሕክምና ተቋማት ውጭ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ ሁሉ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ። በመንግሥት/በግል ድርጅቶች፣ በፋብሪካዎች፣ ...ወዘተ. ለሠራተኞቻቸው የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ፣ የቀይ መስቀል/ቀይ ጨረቃ የሕክምና አገልግሎቶች ...ወዘተ. በዚህ ይካተታሉ። እንዲሁም የሕክምና ባለሙያ ቢሆኑም ባይሆኑም ሕመም በተሰማው ጊዜ ራሱን በራሱ ያከመ በዚህ ይመደባል።

**D.9- How many times did (Name) use the service in the last 2 months?**

**መ.9 - ባለፉት 2 ወራት ውስጥ (እገሌ/ሊት) ለምን ያህል ጊዜ የህክምና አገልግሎት አገኙ?**

ከላይ በጥያቄ ተራ ቁጥር መ.8 ላይ ሲጠየቅ ኀበኘሁት ወይም አገልግሎት አገኘሁበት ላሉት የቤተሰቡ አባላት ባለፉት 2 ወራት ውስጥ ስንት ጊዜ እንደኀበኙት ወይም አገልግሎቱ እንደተጠቀሙ ተጠይቆ ብዛቱ ይመዘገባል። አንድ ሰው የህክምና ተቋሙን ስንት ጊዜ እንደኀበኘው ወይም እንደተገለገለበት የሚቆጠረው አንድ ጊዜ ካርድ አውጥቶ ወይም ከመጀመሪያው ሕክምና ጋር በተያያዘ ሁኔታ የተመላለሰበትን ቀናት (ለውጤት ወዘተ) በመቁጠር ሳይሆን ካርድ ለማውጣት ወይም እንደ አዲስ ለማማከር የሄደባቸውን ቀናት ብቻ በመቁጠር ነው።

**D.10- Did (Name) have any problems at the time of the visit?**

**መ.10 -** (እገሌ/ሊት) በህክምና አገልግሎቱ ወቅት ያጋጠመዎት ችግር ምን ነበር?

የህክምና አገልግሎት ላገኙ የቤተሰብ አባል (በዓምድ 17 አዎን ለመለሱ) በመጀመሪያ በአገልግሎቱ ላይ ችግር አጋጥሞት ወይም ኣላገጠመው እንደሆነ በመጠየቅ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ አዎን ከሆነ ኮድ 1 የለም ከሆነ ደግሞ ኮድ 2 መመዝገብ ያስፈልጋል። ችግር አጋጥሞት ከነበረ ደግሞ የችግሩ ዓይነት/ዓይነቶች ምን እንደሆነ/ኑ በመጠየቅና በመጠይቁ ከተሰጡት ዝርዝር ጋር በማገናዘብ ትክክለኛውን መልስ/መልሶች ይጠቆራል።

ማሳሰቢያ:- በዚህ ክፍል ከአንድ በላይ አማራጭ መልሶች ከተገኙ ሊጠቆር ይችላል። ነገር ግን ችግር አላጋጠመኝም ብሎ "No problem (satisfied)" በሚለው አንፃር ከተጠቆረ ሌላ አማራጭ ማጥቆር አይገባም።

| የችግር/ዓይነቶች ዝርዝር | |
|---|---|
| No problem (satisfied) | ችግር አላጋጠመኝም (በአገልግሎቱ ረክቻለሁ) |
| Facilities were not clean | ንፅህና መጓደል |
| Long waiting time | ረጅም ወረፋ መኖር |
| No trained professionals | የሰለጠነ ባለሙያዎች ያለመኖር |
| Too expensive | የዋጋ መወደድ |
| No drugs available | የመድሃኒት አለመኖር/እጥረት |
| Treatment unsuccessful | የሕክምና አለመሳካት |
| Other | ሌላ |

## D.11- Why did (Name) not use medical care in the last 2 months?

*መ.11* - ባለፉት 2 ወራት ውስጥ (እገሌ/ሊት) በህክምና አገልግሎት ያልተጠቀሙት ለምን ነበር?

በመ.7 ቢታመሙም ባይታሙም ወደ ህክምና ተቋም ወይም ባህል ሐኪም ባለመሄዳቸው ምክንያት "N" የተጠቆረላቸው የቤተሰብ አባላት በዚህ ጥያቄ ወደ ተቋሙ ያልሄዱ ምክንያት ተጠይቆ ከተሰጡት ምርጫዎች ጋር አገናዝቦ በመምረጥ ይጠቆራል። የቤተሰቡ አባል ባለፉት 2 ወራት ውስጥ ያልታመመ ከሆነና ህመም/አደጋ አጋጥሞት የህክምና አገልግሎት ያልወሰደ (ሕመሙ/አደጋው ቀላል በመሆኑ) ከሆነ "No Need" በሚለው ትይዩ ያለው ክብ ይጠቆርለታል። ይሁን እንጂ ታሞ የነበረ የቤተሰብ አባል ወደ ህክምና መስጫ ተቋም ለምን እንዳልሄደ በመጠየቅ ውድ ስለሆነበት ከሆን "Too expensive" በሚለው አንፃር፡ የህክምና ተቋሙ ሩቅ በመሆኑ ምክንያት ከሆነ "Too far" በሚለው አንፃር ዘመናዊም ሆነ ባሕላዊ ሕክምና ያድናል የሚል እምነት የለኝም የሚል ከሆነ "No confidence" በሚለው አንፃር የሚጠቆር ይሆናል። መልስ ሰጪው ከላይ ከተሰረዘሩት ውጭ ሌላ ምክንያት ከጠቀሱ "Other" በሚለው አንፃር ያለውን ትክክለኛ ክብ ይጠቆራል።

ማሳሰቢያ:- በዚህ ክፍል ከአንድ በላይ አማራጭ መልሶች ከተገኙ ሊጠቆር ይችላል። ነገር ግን ህክምና አላስፈለገኝም በሚለው አንፃር ኮድ 1 ከተጠቆረ ሌላ አማራጭ ማጥቆር አይገባም።

| ምክንያቶችና ኮዳቸው | |
|---|---|
| No need | ሕክምና አላስፈለገኝም =1 |
| Too expensive | ውድ ስለሆነ =2 |
| Too far | ሩቅ ስለሆነ =3 |
| No confidence | በህክምናው እምነት ማጣት =4 |
| Other | ሌላ =5 |

## Section E: Employment

## ክፍል ሠ፡ የሥራ ሁኔታ

በዚህ ክፍል የሚሰበሰበውን መረጃ ከጥናቱ ቀን በፊት ከነበሩት 7 ቀናት ወይም 12 ወራት ውስጥ ዕድሚያቸው 5 ዓመትና በላይ ለሆኑ የቤተሰብ አባላት የተከናወኑ የኢኮኖሚ ተግባሮችን የሚመለከቱ ይሆናሉ። መረጃ ሰብሳቢው ይህንን ክፍል ከመሙላቱ በፊት ክፍል "ለ"ን በማየትና ዕድሚያቸው 5 ዓመትና በላይ የሆኑትን በመለየት የቤተሰብ ተራ ቁጥራቸው በማስታወስና በመያዝ ከመጠይቁ አናት ላይ ከተሰጡት የቤተሰብ ተራ ቁጥሮች በማገናዘብ ይጠይቃል።

<u>ምርታማ ሥራ፡</u>- ማለት የሥራው ውጤት የሆነውን ምርት ወይም አገልግሎት በከፊል ወይም በጠቅላላ በገንዘብ ወይም በዓይነት በመለወጥ ገቢ ለማግኘት ለገበያ ለማቅረብ ሲቻል ነው። ይህም ማለት በራስ፣ በቤተሰብ ይዞታ፣ በመንግሥታዊ፣ በሕዝባዊ ወይም በግለሰብ ድርጅት፣ በቀን፣ በሣምንት፣ በወር ወይም በስሩት መጠን ክፍያ ወይም ገቢ ለማግኘት ሥራ ሲሰሩ ነው።

በምርታማ ሥራ ውስጥ የሚጠቃለሉ የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት ተግባራት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል:-

ሀ. ትርፍ ለማስገኘት ዕቃዎችን ማምረት ለምሳሌ የፋብሪካ ውጤቶች፣ የሸክላ ሥራ፣ ...ወዘተ ወይም አገልግሎቶችን ማቅረብ ለምሳሌ ፀጉር ማስተካከል፣ የሽመና ሥራ፣ የአረቄ ንግድ ...ወዘተ፣

ለ. ለመንግሥት፣ ለሌላ ድርጅት ወይም ለግለሰብ በክፍያ የሚሰሩ ሥራዎች (ለምሳሌ ሕክምና፣ ትምህርት፣ ...)፣ በተጨማሪ ያለክፍያ ለመረዳዳት ወይም በዘመቻ የሚሰሩ (ለምሳሌ ምግብ ለሥራ፣ የደን ተከላ፣ የደቦ ሥራ ... ወዘተ)፣

ሐ. ለራስ የምግብ ፍጆታ ወይም ለሽያጭ ወይም ቋሚ ንብረት ለማከማቸት ሲባል የማምረት ተግባር እነርሱም:-

1. ለራስ የምግብ ፍጆታ ሲባል ቀዳሚ ውጤቶችን (Primary Products) የማምረት ተግባር፣ ለምሳሌ የተለያዩ ሰብሎች (ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬ፣ ጥጥ፣ ...ወዘተ) ማምረት፣
2. ከላይ (በተራ ቁጥር 1) ያመረቱትን ምርት ወደ ሌላ ዓይነት ምርት የመለወጥ ተግባር፣ ለምሳሌ ፈትል መፍተል ወይም ሌላ ቁሳቁሶችን ለሽያጭ ማዘጋጀት፣

3. ለራስ የምግብ ፍጆታ የሚመረቱ፣ ለምሳሌ ጠላ ጠምቀው (ከራሱን ቢጠጡም) የሚሸጡ፡፡

4. ቋሚ ንብረቶችን (ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያህል ግልጋሎት መስጠት የሚችሉ) ለራስ ጥቅም ሲባል ማምረት፣ ለምሳሌ የራስን ግቢ ወይም አካባቢ ግንቧታ፣ የእርሻ ውጤት ማከማቻ መጋዘኖችንና የእርሻ መሣሪያዎችን መሥራት፣ ሌሎች መሣሪያዎችን ማምረት ናቸው፡፡

4. በክፍያ ለቤተሰብ ግልጋሎት የሚውሉ ሥራዎችን መሥራት (ልጆች ማስተማር፣ የቤት ሠራተኛነት ሥራ፣ ...ወዘተ)

ከላይ የተገለፁትን ምርቶች በማምረትና ግልጋሎት በማቅረብ ተግባር ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች በምርታማ ሥራ ላይ እንደተሰማሩ ይቆጠራል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት የማምረት ወይም ግልጋሎት የመስጠት ተግባራት ውስጥ ሊጠቃለሉ የማይችሉ ሥራዎች በጠቅላላ ምርታማ ያልሆኑ ሥራዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡ የቤተሰቡ አባላት ያለ ክፍያ ለቤተሰብ ግልጋሎት የሚውሉ ሥራዎችን ለምሳሌ <u>ልጆችን ማስተማር፣ ማሳደግ፣ ቤተሰቡ የሚመገበውን ምግብና መጠጥ ማዘጋጀት፣ የራሳቸውን አጥር፣ ቤት ...ወዘተ</u> አነስተኛ የጥገና ተግባር ማከናወን፣ በበጎ ፈቃደኛነት ለአካባቢው ኅብረሰብ በተለያዩ ማኀበራዊ (ሌላ ሥራ እያላቸው) ግልጋሎት መስጠት ...ወዘተ እንደምርታማ ሥራ አይቆጠሩም፡፡ ሆኖም ከላይ የተገለፁት የቤት ውስጥ ሥራዎች ለክፍያ ተብለው እስከተከናወኑ ድረስ በምርታማ ሥራ ክፍል ይመደባሉ፡፡ በልመና፣ ሴተኛ አዳሪነት (መጠጥ ደርድረው ሆነ ሳይደረድሩ) የሚተዳደሩ ምርታማ ሥራ እንደሚሰሩ አይቆጠሩም፡፡ የቡና ቤት አሻሻጮች፣ በሴተኛ አዳሪነት ተግባር ከተሰማሩ ምርታማ ሥራ እንደሰሩ አይቆጠሩም፡፡ ነገር ግን በቡና ቤት ውስጥ ተቀጥረው የሚያገለግሉ ሌሎች ሠራተኞች ለምሳሌ አልጋ አንጣፊ፣ ገንዘብ ተቀባይ፣ ቡናና ሻይ የሚያፈሉ (ባሬስታ)፣ ወጥ ቤት፣ የቡና ቤት ባለቤቶች፣ በትላልቅ ሆቴሎች በአስተናጋጅነት ተቀጥረው የሚሰሩትን በመርታማ ስራ እንደተሰማሩ ይቆጠራሉ፡፡ በተጨማሪም ሳይከፈላቸው የሥራ ልምምድ (በቢሮ፣ በጋራዥ፣ ...ወዘተ) የሚያደርጉ የሚሰሩት ሥራ እንደ ምርታማ ሥራ ይቆጠራል፡፡

## E.1 Did (Name) do any type of work in the last 7 days?

## ሠ.1 ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ (እገሌ/ሊት) በምርታማ ሥራ (ለክፍያ፣ ለትርፍ ወይም ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ) ተሰማርተው ነበርን?

በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው የቤተሰቡ አባላት ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ከላይ የቀረበውን የምርታማ ሥራ ትርጉም በሚያሟላ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ነው፡፡ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ በምርታማ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ለመለየት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚከተሉትን ዋና ዋና የሥራ ዘርፎችን የያዘ ማጣሪያዎች መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም፡-

- በመንግሥት ወይም በግል ድርጅት ተቀጥረው ሠርተዋል?
- በንግድ ሥራ ተሠማርተው ነበር?
- በቅጥርም ሆነ በግል በክፍያ አገልግሎት በመስጠት ተሰማርተው ነበር?

- በግብርና ሥራ ተሰማርተው ነበር?
- ለሽያጭ የሚሆኑ ዕቃዎች አምርተው ነበር?
- ለቤተሰቡ ቋሚ ንብረት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ሰርተው ነበር?
- ያለ ክፍያ ለቤተሰብዎ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ተሰማርተው ነበር?
- ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ ሌላ ምርታማ ሥራ ሰርተዋልን? ለምሳሌ፦ በተለማማጅነት

ከነዚህ የሥራ ዘርፎች በአንዱ እንኳን ከተሳተፈ በምርታማ ተግባር እንደተሠማራ ተቆጥሮ "Y" ተብሎ የተከበበውን ማጥቆር ሲገባ ካልተሳተፈ/ች ደግሞ "N" የሚለው ይጠቆራል:: እዚህ ላይ "Y" የሚለው ከተከበበ በቀጥታ ወደ ጥያቄ ተራ ቁጥር ሠ.6 ማለፍ ይገባል::

**E.2 Was (Name) temporarily absent from work in the last 7 days?**

ሠ.2 (እገሌ/ሊት) ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ሥራ ያልሰሩት ሥራ እያለዎት ነው?

ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ባለፉት 7 ቀናት ሥራ ላልሠሩ ማለትም በጥያቄ ተራ ቁጥር ሠ.1 "N" ለተጠቆረላቸው የቤተሰቡ አባላት ሲሆን በዚህ ጥያቄ ላይ ሥራ እያላቸው ቀሪ ለሆኑ "Y" የሚለው የሚጠቆር ሲሆን የቤተሰቡ አባል ሥራ ከሌለው ግን "N" በሚለው እንዣር ይጠቆራል:: እዚህ ላይ ከስራቸው ቀሩ የሚባሉ ሰዎች ባለፉት 7 ቀናት በዓመት ፈቃድ፣ በወሊድ ፈቃድ፣ በሕመም፣ በትምህርት ወይም ስልጠና ላይ ስለሆኑ፣ ለጊዜው ሥራው በተለያየ ምክንያት ስለቆመ (ለምሳሌ ዕድሳት፣ የጥሬ ዕቃ እጦት፣ የመብራት አለመኖር የመሳሰሉት) ያልሠሩ ግን ችግሩ ሲቃለል ወይም ጉዳያቸው ሲያበቃ ወደ ሥራቸው የሚመለሱ መሆን አለባቸው::

## ከሥራቸው የቀሩ ሰዎች

1. በቅጥር ለሚሰሩ በቀሩበት ወቅት ሙሉ ወይም ከፊል ክፍያ የሚያገኙ፣ ወይም
2. በቅጥር ለሚሰሩ ከሥራ ያስቀራቸው ምክንያት ሲቃለል ወደ ቀድሞ ሥራቸው የሚመለሱ ወይም
3. በቅጥር ለሚሠሩ ከሥራ ከቀሩ 2 ወር ያልሞላቸው መሆን አለባቸው፡፡
4. በግል ለሚተዳደሩ እነሱ ከሥራ ቢቀሩም ድርጅታቸው ያልተዘጋ (ተመልሶ የሚከፈት) መሆን አለበት::

ማስታወሻ፦ ለቤተሰባቸው ያለ ክፍያ የሚሠሩ እና የቀን ሠራተኞች በጥናቱ ሳምንት ባይሠሩ "ሥራ እያላቸው ከሥራ የቀሩ" ተብለው አይጠቆሩም::

**E.3 Did (Name) do any type of work in the last 12 months?**

**ሠ.3 ባለፉት 12 ወራት (እገሌ/ሊት) አብዛኛውን ጊዜ በምርታማ ሥራ (ለክፍያ፣ ለትርፍ ወይም ለቤተሰብ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ) ተሰማርተው ነበርን?**

በዚህ ጥያቄ ለማወቅ የተፈለገው የቤተሰቡ አባላት ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ከላይ የቀረበውን የምርታማ ሥራ ትርጉም በሚያሟላ ተግባር ላይ መሠማራት አለመሠማራታቸውን ነው:: በጥያቄ ተራ ቁጥር ሠ.1 እና ሠ.2 "N" የተጠቆረላቸው የቤተሰቡ አባላትም ከጥናቱ ቀን በፊት ካለው ቀን ጀምሮ ባለፉት 12 ወራት ውስጥ በአብዛኛው በምርታማ ሥራ ተሰማርተው እንደነበር ይጠየቃሉ:: በአብዛኛው ተሠማርተው ከነበረ "Y" ተብሎ የተከበበው የሚጠቆር ሲሆን፣ ካልሠሩ ግን በሚለው አንፃር "N" የሚለው ኮዱ ይጠቆራል::

<u>ማሳሰቢያ:-</u> የስራ ሁኔታ በተመለከተ የ12 ወራት ሁኔታ መረጃ በጥያቄ ሠ.3 እንደሚያበቃ ይታወቅ::

አንድ ግለሰብ ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ሰርቷል የሚባለው በተሰማራበት የሥራ መስክ/ኮች ከ6 ወራት (ማለትም ከ26 ሳምንታት) በላይ ምርታማ ሊያስኝ የሚችል ሥራ ከሰራ ነው:: ይህ አጠቃላይ ትረጉሙ ሲሆን ሰዎች ከተሰማሩባቸው የተለያዩ የሥራ መስኮች ፀባይና አጠቃላይ ትርጉምን ከየአገሩ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አዛምዶ ከመጠቀም አኳያ ከመሠረታዊ ትርጉም ጋር ሊጣጣም በሚችል መልኩ ዘርዘር ያሉ የአሰራር መመሪያዎች ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ ዝርዝሩ ከዚህ በታች ተመልክቷል::

ሀ. አንድ በእርሻ ሥራ የተሰማራ ግለሰብ (በገጠር) ባለፉት 12 ወራት አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ሰርቷል የሚባለው በአካባቢው በሚታወቀው በአንድ የሰብል ዘመን አብዛኛውን ጊዜ ከሰራ ነው:: ለምሳሌ የአካባቢው አንድ የሰብል ዘመን 8 ወራት ከሆነና ግለሰቡ ለ4 ወራትና ከዚያ በላይ የግብርናውን ሥራ ከሰራ ምርታማ ሥራ እንደሰራ ይቆጠራል:: አንድ የሰብል ዘመን የሚባለው የመኸሩንና የበልጉን ወቅቶች የሚያጠቃልል ሲሆን የሚከናወኑትም ሥራዎች የኩትኳቶው፣ የአጨዳው፣ የመሰብሰቡን... ወዘተ ጊዜ ያጠቃልላል፡

ለ. በሌላ ግብርና ማለትም:- በከብት እርባታ፣ ንብ እርባታ፣ ...ወዘተ የተሰማሩ ግለሰቦች በተሰማሩበት የሥራ መስክ/ኮች ባለፉት 12 ወራት 6 ወራትና በላይ (በገጠሩ) ከሰሩ ምርታማ ሥራ እንደሰሩ ይቆጠራሉ፡

ሐ. በሌሎች የሥራ መስኮች ማለትም ንግድ፣ ሽመና፣ አንጥረኝነት፣ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ...ወዘተ የተሰማሩ ግለሰቦች በተሰማሩበት የሥራ መስክ/ኮች ባለፉት 12 ወራት ለ6 ወራትና በላይ ከሰሩ ምርታማ ሥራ እንደሰሩ ይቆጠራሉ።

**E.4 Has (Name) been looking for work and ready for work in the last 4 weeks?**

**ሠ.4 (እገሌ/ሊት) ባለፉት 4 ሳምንታት ውስጥ ሥራ ለማግኘት ጥረት አድርገው ነበርን?**

እዚህ ላይ ከላይ ለተጠየቁት ጥያቄዎች (ሠ.3) "N" ተብሎ የተጠቆረላቸው የሚጠየቁ ሲሆን ባለፉት 4 ሳምንታት ውስጥ ሥራ ለመስራት ተዘጋጅተውና ሥራ ለማግኘት ጥረት አድርገው ለነበሩት "Y" የሚለው ክብ በተራ ቁጥራቸው አንፃር ይጠቆራል። ነገር ግን ጥረት ላላደረጉት ግን "N" የሚለውን ክብ ማጥቆር ያስፈልጋል። በተጨማሪም የሚቀጥለውን ጥያቄ ሠ.5 ራሱን የቻለ ስለሆነ ጥረት ላደረጉም ሆነ ላላደረጉ መጠየቅ ተገቢ ነው።

<u>ማስታወሻ፡</u>- አንድ ግለሰብ ሥራ ለማግኘት ጥረት አድርጎ ነበር የሚባለው ባለፉት 4 ሳምንታት ውስጥ ቢያንስ የሥራ አጥ ካርድ አውጥቶ ከነበረ፣ ወይም የሥራ ማመልከቻ ለመስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ካስገባ ወይም የሥራ ማስታወቂያዎችን ከጋዜጣ፣ ከሬድዮ፣ ከጓደኛ ወይም ከተለያዩ ቦታዎች ተከታትሎ ከሆነ ወይም የግል ሥራ ለመጀመር ሙከራ ካደረገ፣ ...ወዘተ ነው።

**E.5 What was the main reason (Name) was not working in the reference period?**

**ሠ.5 ባለፉት 7 ቀናት (እገሌ/ሊት) ሥራ ያልሠሩበት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?**

በምርት ተግባር ላይ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ላላደረጉት ወይም በጥያቄ ሠ.1 አቅጣጫ "N" ለተጠቆረላቸው ያልሰሩበት ምክንያት በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ያልሰሩበት ምክንያት ጋር በማዛመድ ማጥቆር ያስፈልጋል።

| ያልሰሩበት ዋና ምክንያት ዝርዝር | | ኮድ |
|---|---|---|
| No work available | ሥራ ስለሌለ | 1 |
| Seasonal inactivity | የሥራ ወቅት ባለመሆኑ | 2 |
| Student | ተማሪ (ትምህርት/ስልጠና) | 3 |
| Household/family duties | የቤት ውስጥ ሥራ | 4 |
| Too old/Too Young | እርጅና/ልጅ በመሆኑ | 5 |
| Disability/Ill health | አካል ጉዳተኝነት/ህመም | 6 |
| Other | ሌላ | 7 |

1. ስራ ስለሌለ:- እነዚህ ግለሰቦች ሥራ ከማጣታቸው የተነሳ ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ምርታማ ሥራ ያልሰሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ሥራ ለማግኘት ሙከራ ያደረጉም ያላደረጉም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሥራ ካገኙ ለመስራት ዝግጁ የነበሩ ናቸው፡፡

2. የሥራ ወቅት ባለመሆኑ:- እነዚህ ግለሰቦች ምንም እንኳን ስራ ሰርተው የሚያውቁ ቢሆንም ሥራ ከማጣታቸው የተነሳ ባለፉት 7 ቀናትም ሆነ 12 ወራት ምርታማ ሥራ ያልሠሩ፣ ነገር ግን የሥራ ልምድ ያላቸው ሥራ አጦች ናቸው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ሥራ ለማግኘት ሙከራ ያደረጉም ያላደረጉም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሥራ ካገኙ ለመስራት ዝግጁ የነበሩ ናቸው፡፡

3. ተማሪ:- በዚህ ኮድ የሚካተቱት ትምህርት ከመከታተላቸው የተነሳ ባለፉት 7 ቀናት በምርታማ ሥራ ላይ ያልተሠማሩ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎች ሆነው ምርታማ ሥራ ሰርተው ከሆነ ወደ እዚህ አይመጡም፡፡

4. የቤት ውስጥ ሥራ:- ይህ የሚያመለክተው ክፍያ ሳያገኙ ለቤተሰቡ ግልጋሎት በመስጠት ብቻ የነበሩትን ነው፡፡ ለምሳሌ. የቤት እመቤት፣ ልጆችን ያካትታል፡፡

5. ሽማግሌ/አሮጊት ወይም ለሥራ ያልደረሱ:- እዚህ ላይ ሥራ ያልሰሩበት ምክንያት በዕድሜ መግፋት ወይም ዕድሜያቸው ለሥራ ያልደረሱ ተብሎ የተነገረ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

6. አካል ጉዳት/ህመም:- የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ወይም በህመም ምክንያት ባለፉት 7 ቀናት ምንም ሥራ ያልሠሩ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ሥራ እንዳይሠሩ ያገዳቸው ምክንያት በሽታቸው/አካል ጉዳተኝነታቸው ከሆነ ብቻ ነው፡፡

7. ሌላ ምክንያት:- ሴተኛ አዳሪ፣ እስረኛ የነበረ፣ ...ወዘተ ሌላ በሚለው ስር ይጠቃለላሉ፡፡

ው.6-ው.10 ባለፉት 7 ቀናት ሥራ ለሠሩ (ው.1 "Y") ለተጠቆረላቸው የሚጠየቅ

**E.6 How many jobs did (Name) have in the reference period?**

**ው.6 ባለፉት 7 ቀናት (እገሌ/ሊት) ስንት የተለያየ ዓይነት ሥራ ሰርተዋል?**

በጥያቄ ው.1 ላይ በሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ግለሰቦች በተሠማሩበት ወቅት ስንት ዓይነት ሥራ እንደሠሩ ተጠይቆ አንድ ዓይነት ከሆነ "1" ሁለት ዓይነት ከሆነ "2" ሁለትና ከዛ በላይ ከሆነ ደግሞ "3" ተብሎ የተከበበው ይጠቆራል።

**E.7 What is (Name) Employment status in the main job?**

**ው.7 የ(እገሌ/ሊት) ዋነኛ ሥራ የቅጥር ሁኔታ ምንድን ነው?**

በዚህ ጥያቄ በምርታማ ሥራ ላይ ተሠማርተው የነበሩት ሰዎች የዋነኛ ሥራቸውን ማለትም ይበልጡን ጊዜ ያሳለፉበትን የሥራ ዓይነት መሠረት በማድረግ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ስድስት ዓይነት የቅጥር ሁኔታዎች ውስጥ ትክክለኛውን በመለየት ተስማሚውን ኮድ ማጥቆር ያስፈልጋል።

| የቅጥር ሁኔታ ዝርዝር | | ኮድ |
|---|---|---|
| Employee | ቀጣሪ | 1 |
| Self-employed | በግል ሥራ የሚተዳደር | 2 |
| Paid employed | ተቀጣሪ (በክፍያ) | 3 |
| Paid domestic service | ተቀጣሪ የቤት ውስጥ ሥራ | 4 |
| Unpaid contribution worker | ሳይከፈላቸው ለቤተሰብ የሚሠሩ | 5 |
| Other | ሌላ | 6 |

1. ቀጣሪ:- በራሱ ድርጅት ውስጥ ቢያንስ አንድ ሰው ቀጥሮ በማሰራት የሚተዳደር ቀጣሪ ይባላል። ቀጥረው የሚያሰሩ ሁሉ በሥራው ላይ አብረው ቢሰማሩም እንደ ቀጣሪ ይቆጠራሉ።

2. በግል ሥራ የሚተዳደር:- በግል ሥራ ወይም ድርጅታቸው ውስጥ የሚሠሩ ነገር ግን ምንም ተቀጣሪ የሌላቸው ናቸው። የቤተሰብ አባላትን ያለ ክፍያ በማስተባበር ሥራቸውን የሚያካሂዱ ኃላፊዎች በዚህ ኮድ ይካተታሉ።

3. <u>ተቀጣሪ፡-</u> በማንኛውም ዓይነት የግል ድርጅት (መደበኛ በሆነም ይሁን ባልሆነ የሥራ ዘርፍ)፣ መንግስታዊ በሆነ ድርጅት ወይም መንግስታዊ ልሆነ ድርጅት ተቀጥረው በክፍያ የሚሠሩ ከሆነ በዚህ ይጠቃለላሉ።

4. <u>ተቀጣሪ ለቤተሰብ/ለግለሰብ፡-</u> እየተከፈላቸው ቤተሰቡን በማገልገል ላይ የሚገኙ የቤት ሠራተኞች፣ ዘበኞች፣ አትክልተኞች፣ የቤተሰቡ ሾፌሮች ...ወዘተ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ። እነዚህ ሰዎች በማገልገል የሚገኙት የቤተሰቡን ድርጅት ሳይሆን ቤተሰቡ ራሱን መሆን ይኖርባቸዋል።

5. <u>ሳይከፈላቸው ለቤተሰቡ ድርጅት የሚሠሩ፡-</u> ያለ ምንም ክፍያ በቤተሰቡ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ናቸው።

6. <u>ሌላ፡-</u> ከተዘረዘሩት የቅጥር ሁኔታዎች በአንዱም ሊካተት ያልቻለ በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ። ለምሳሌ ሳይከፈላቸው ሥራ የሚለማመዱ፣ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ለሕዝባውያን ድርጅቶች፣ ለሃይማኖት ድርጅት የሚሰሩና ምንም ክፍያ የማይሰጣቸው።

## E.8 For whom did (Name) work in the main job?

*ሠ.8 (እገሌ/ሊት) ዋነኛ ሥራውን/ሥራዎን የሚያከናውኑት ለማን ነው?*

ይህ ጥያቄ ግለሰቦቹ የሚሠሩት ለማን እንደሆነ የሚጠየቁበት ሲሆን ከተሰጡት ስድስት አማራጭ ኮዶቹ ውስጥ ትክክለኛውን ለይቶ ማጥቆር ያስፈልጋል። ከነዚህም ውስጥ በማንኛውም መንግስታዊ በሆነ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ኮድ "1"፣ በግል ድርጅት መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ የሚሰሩ ኮድ "2" በግል ድርጅት መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሚሠሩ ኮድ "3"፣ ያለክፍያ ለቤተሰቡ ድርጅት የሚሠሩ ኮድ "4"፣ መንግስታዊ ባልሆነ የግብረ ሰናይ/የዕርዳታ/፣ የልማት ድርጅቶች፣ የተለያዩ የውጭ መንግስታት፣ የተባበሩት ምንግስታት ...ወዘተ ውስጥ የሚሠሩ ኮድ "5" የሚጠቆርላቸው ሲሆን ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከተገኙ በኮድ "6" ይካተታሉ።

| | ለማን ነው የሚሰሩት? | ኮድ |
|---|---|---|
| Government | ለመንግስት | 1 |
| Private business (formal) | ለግል ድርጅት መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ | 2 |
| Private business (informal) | ለግል ድርጅት መደበኛ ባልሆነ የሥራ ዘርፍ | 3 |
| Private person or household | ለግለሰብ/ለቤተሰብ | 4 |
| NGO | መንግስታዊ ላልሆነ ድርጅት | 5 |
| Other | ሌላ | 6 |

ማስታወሻ፡- በግል ድርጅት መደበኛ በሆነ የሥራ ዘርፍ የሚባለው የንግድ/የሥራ ፈቃድ ያለው ድርጅት ሲሆን የንግድ/የሥራ ፈቃድ የሌለው ከሆነ ግን መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ የተሰማራ የግል ድርጅት ይባላል።

## E.9 What is the main activity at the place of (Name) main job?

*ሠ.9 (እገሌ/ሊት) ዋንኛነት የሚሠሩበት ድርጅት ዋና ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነት ምንድን ነው?*

በዚህ ጥያቄ ግለሰቡ የሚሰራበት ድርጅት የሚያመርተው ምርት ወይም የሚሰጠው አገልግሎት በመጠየቅ ከተሰጡት ዘጠኝ አማራጭ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ውስጥ ሊካተት የሚችልበትን ተስማሚ ኮድ በመምረጥ ማጥቆር ያስፈልጋል። ድርጅት ሲባል የተለየ ክፍል ወይም ቦታ ሳይኖራቸው በመኖሪያ ቤት ውስጥ በበረንዳ፣ በትናንሽ ገበያዎች/ጉልቶች በመንገድ ላይ ...ወዘተ ከሚከናወኑ ጥቃቅን ሥራዎች አንስቶ የተለየ አድራሻና አደረጃጀት ያላቸውን ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎችን ያጠቃልላል። በሌላ መልኩ በዚህ ጥያቄ የሚፈለገው ለምሳሌ በባንክ ድርጅት ውስጥ የምትሰራ ፀሐፊ የኢንዱስትሪ ምደባ ባንክ/ኢንሹራንስና የኪራይ አገልግሎት በሚለው ስር ስትመደብ፣ ነገር ግን በትራንስፖርት ድርጅት ውስጥ የምትሰራ ፀሐፊ ትራንስፖርትና መገናኛ በሚለው የኢንዱስትሪ ምደባ መካተት ይኖርባታል።

| የድርጅቱ ዋና ምርት/አገልግሎት (የኢንዱስትሪ ዘርፍ) ዝርዝር | | ኮድ |
|---|---|---|
| Agriculture | ግብርና | 0 |
| Mining/Quarrying | ማዕድን ድንጋይና አሸዋ ማውጣት | 1 |
| Manufacturing | ማምረት (ማኒፋክቸሪንግ) | 2 |
| Construction | ኮንስትራክሽን (ግንባታና መሠል ተግባራት) | 3 |
| Electricity/Gas/Water | ኤሌክትሪክ፣ ጋዝና ውሃ አቅርቦት | 4 |
| Distributive Services | የጅምላና ችርቻሮ ንግድ | 5 |
| Transport & Communication | ትራንስፖርትና መገናኛ | 6 |
| Bank/Insurance/Real State | ባንክ/ኢንሹራንስና የቤት ኪራይ | 7 |
| Public administration/defense | የመንግስት አስተዳደርና የመከላከያ አገልግሎት | 8 |
| Other | ሌላ | 9 |

የድርጅቱን ዓይነት ከማጥቆራችን በፊት የግለሰቡ ድርጅት በየትኛው እንደሚካተት ለማወቅ ከዚህ በታች የቀረበውን ዝርዝር ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል።

0. <u>ግብርና</u>

በዚህ ክፍል የሚጠቃለሉት የእርሻ ምርት የሚያመርቱ፣ የቤት እንስሳት (ከብት፣ ዶሮና፣ ንብ፣ ወዘተ) የሚያረቡ፣ የግብርና ነክ አገልግሎት የሚሰጡ፣ የደን ሀብት ምርት የሚያመርቱ፣ ዓሣ በማስገር የተሰማሩ ድርጅቶችን በሙሉ ያካትታል።

1. <u>ማዕድን ድንጋይና አሸዋ ማውጣት</u>

የድንጋይ ከሰል የሚመርቱ፣ ያልተጣራ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ የሚያመርቱ፣ ዘይትና ጋዝ በመፈለግ የሚደረጉትና ተመሳሳይ አገልግሎቶችን የሚሰጡ፣ ብረት ነክ የሆኑና ያልሆኑ ማዕድናትን የሚያመርቱ፣ ሌሎች የድንጋይና የአሸዋ ማውጣት ሥራ የሚሰሩትን ያጠቃልላል።

2. <u>ማምረት (ማኒፋክቸሪንግ)</u>

ማምረት (ማኒፋክቸሪንግ) ማለት አንድን ዕቃ ወደ ሌላ አዲስ ዓይነት ዕቃ ወይም ምርት የመለወጥ ተግባር ነው። ስለዚህ በዚህ የማምረት መለያ ኮድ ውስጥ የሚካተቱት፤ የምግብ ውጤቶችን የሚያመርቱ (በእጅ ወይም በፋብሪካ ሊሆን ይችላል)፣ ትምባሆና መጠጦችን የሚያመርቱ፣ ጨርቃ ጨርቅ ወይም የሚለበሱ ልብሶችን የሚያመርቱ፣ ከፀጉር የሚሰሩ ልብሶችን በማቅለም የሚያዘጋጁ፣ ቆዳ በማልፋት በማለስለስ የሚያዘጋጁ፣ የእንጨት ውጤቶችን የሚያመርቱ፣ ወረቀትና የወረቀት ውጤቶችን የሚያመርቱ፣ የማተም የመጠረዝና የማባዛት (ፊልም፣ ሪከርዶችን ...ወዘተ ሊሆን ይችላል) ሥራ የሚሰሩ፣ የተጣራ የነዳጅ ውጤቶችን የሚያመርቱ ...ወዘተ እና ሌሎች በማምረት ተግባር የተሠማሩትን በሙሉ ያጠቃልላል።

3. <u>ኮንስትራክሽን</u>

በዚህ ክፍል ህንፃዎች/መኖሪያ ቤቶችን/መንገዶችን/ድልድዮችና የመሳሰሉትን የመገንባት ሥራ የሚሠሩ፣ በህንፃዎች ላይ የኤሌክትሪክ ውሃና ሌሎች የመገጣጠም ሥራን የሚሰሩ፣ የህንፃ መስሪያ መሣሪያዎችን የሚያከራዩ ድርጅቶችን ያጠቃልላል።

4. <u>ኤሌክትሪክ፣ ጋዝና ውሃ አቅርቦት</u>

የኤሌክትሪክ፣ ጋዝ፣ እንፋሎትና ሙቅ ውሃ አቅርቦት፣ ውሃ ማከማቸት፣ ማስራጨትና የማከፋፈል አገልግሎት የሚሰጡ በዚህ ይካተታሉ።

5. <u>የማከፋፈል አገልግሎት (የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ...ወዘተ)</u>

በዚህ ምድባ ኮድ የሚመደቡ ድርጅቶች የጅምላ ንግድና ችርቻሮ ንግድ ላይ የተሰማሩ፤ የመኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች ሽያጭና ጥገና የሚያከናውኑ፤ የግልና የቤት ውስጥ ዕቃዎችን የሚጠግኑ፤ የሆቴል እና የምግብ ቤት አገልግሎት የሚሰጡ ... ወዘተ ናቸው።

## 6. ትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎት

በየብስ፤ በአየር ወይም በውሃ ላይ ሰውን፤ ዕቃን፤ ...ወዘተ የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ፤ የሸክም ሥራ የሚሠሩ፤ ከትራንስፖርት ጋር ግንኙነት ያላቸውን አጋዥ ሥራዎች (የጉዞ ወኪል፤ የመጋዘን አገልግሎት፤ ...ወዘተ) የሚሰሩ፤ የፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጡ በዚህ ክፍል ይመደባሉ።

## 7. ባንክ/የመድህን አገልግሎትና የሪል እስቴት (የማከራየት አገልግሎት)

የፋይናንስ/የገንዘብ እንቅስቃሴን፤ የመድህን እንቅስቃሴንና ግንኙነት ያላቸው ሥራዎች የሚሰሩ፤ የማይንቀሳቀስ ንብረት፤ ማሽኖችን፤ የቤትና የቢሮ ዕቃዎች እና ሌሎች ያልተጠቀሱ ዕቃዎችን በሚያከራየት አገልግሎት የሚሰጡ፤ ኮምፒዩተርና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎች የሚሰሩ፤ የማስታወቂያ፤ ህግ ነክ እና ሌሎች የማማከር ሥራ የሚሰሩ በዚህ ክፍል ይካተታሉ።

## 8. የመንግስት አስተዳደርና መከላከያ አገልግሎት

ሁሉን አቀፍ ግልጋሎት ለህብረተሰቡ የሚሰጡ የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች (ከቀበሌ እስከ ሚኒስቴር ደረጃ ድረስ) የሚሰሩ፤ የፀጥታ እና የአገር መከላከል ሥራ የሚሰሩ፤ የማህበራዊ ዋስትና (ጡረታ) አገልግሎት ሥራ የሚሠሩ፤ የህብረተሰቡን የኢኮኖሚና ፖሊሲዎች የሚቀይሱ፤ በዚህ ክፍል ይካተታሉ።

## 9. ሌሎች

ከላይ ከኮድ 0-8 ያልተጠቀሱ ድርጅቶችና አገልግሎት ሰጪዎች በዚህ ኮድ ይጠቃለላሉ። ለምሳሌ እለም አቀፍ እና እህጉራዊ ሥራ የሚሰሩ፤ የህብረተሰቡን የትምህርት፤ የጤና፤ የባህል ስፖርትና ማህበራዊ ጉዳዮች የመከታተልና የማካሄድ ሥራ የሚሰሩ፤ ለቤተሰብ ግልጋሎት ቅጥር ሠራተኞችን የሚያሰሩ፤ ...ወዘተ ናቸው።

**E.10 Did (Name) seek to increase his or her earnings in the last 7 days?**

**ሠ.10 ባለፉት 7 ቀናት (እገሌ/ሊት) ገቢውን/ገቢዋን ለማሳደግ ያደረጉት ጥረት ነበርን?**

በዚህ ጥያቄ ሥራ ላይ የነበሩ ሰዎች ገቢያቸውን ለማሳደግ ወይም ለመጨመር ያደረጉት ጥረት ካለ ይጠየቃሉ። ከዛም ጥረት ላደረጉት "Y" ተብሎ የተከበበው ይጠቆርና

ወደሚቀጥለው ጥያቄ ሠ.11 ሲታለፍ ጥረት ላላደረጉት ደግሞ "N" በሚለው እንዣር ይጠቆርላቸውና ወደሚቀጥለው ክፍል ይታለፋል።

**E.11 How did (Name) seek to increase earnings in the last 7 days?**

ሠ.11 ባለፉት 7 ቀናት (እገሌ/ሊት) ገቢውን/ዋን ለማሳደግ የተደረገ ጥረት ካለ ምን ነበር?

ከላይ ለጥያቄ ሠ.10 አዎ "Y" ብለው ለመለሱ ሰዎች ገቢያቸውን በምን ዓይነት መንገድ ለማሳደግ ጥረው እንደነበር ይጠየቃሉ። ከዚያም በያዙት ሥራ ተጨማሪ ሰዓትን በመስራት (More hours current activity) ከነበረ ኮድ "1" ሲጠቆርላቸው፣ ከያዙት ሥራ ውጭ ተጨማሪ ሰዓት ሌላ ሥራ በመስራት (More hours additional activity) ከነበረ ኮድ "2"፣ የያዙትን ሥራ በመቀየር ሌላ የተሻለ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ በመስራት (Change activity) ከነበረ ኮድ "3" እና ከነዚህ ውጭ በሌላ መንገድ ከነበረ ሌላ (Other) ኮድ "4" የሚለው ይጠቆርላቸዋል።

## Section F: Household Assets

## ክፍል ረ: የቤተሰቡ የቋሚ ንብረት ሁኔታ

በዚህ ክፍል የሚሞላው እያንዳንዱን የቤተሰብ አባላት በተመለከተ ሳይሆን በአጠቃላይ ቤተሰቡን በማስመልከት የሚሞላ መጠይቅ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

**F. 1 Does the household or a household member own the dwelling?**

**ረ .1 የቤተሰቡ መኖሪያ ቤት የቤተሰቡ ወይም የቤተሰቡ አባል ነውን?**

ቤተሰቡ ወይም የቤተሰቡ አባል በጥናቱ ወቅት የሚኖርበት ቤት የራሱ መሆን አለመሆኑን በመጠየቅ መኖሪያ ቤቱ የቤተሰቡ አባል ከሆነ ኮድ "1" የሚጠቆር ሲሆን የራሱ መኖሪያ ቤት ካልሆነ ደግሞ የቤቱ ይዞታ አይነት ምን እነደሆነ በመጠየቅ ከተዘረዘሩት አማራጭ ኮዶች መካከል የተገቢውን መልስ ኮድ/ኮብ ይጠቆራል::

<u>አማራጭ ምክንያትና ኮድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| Owns the dwelling | 1 | የግል መኖሪያ ቤት ነው |
| Rent the dwelling from Govt. | 2 | ከመንግሥት የተከራየው |
| Rents the dwelling from Private | 3 | ከግለሰብ የተከራየው |
| Uses without Paying rent | 4 | በነፃ የተገኘ |
| Other | 5 | ሌላ |

<u>ቤት</u> ሲባል ዙሪያውን ከወለል እስከጣሪያ ድረስ አንድ አዋቂ ሰው ለማስቆም በሚደርስ ግድግዳ የተከበበና ቢያንስ አራት ካሬ ሜትር የሆነ ቦታ ሆኖ ስፋቱ ለአንድ አዋቂ ሰው አልጋ ለማስዘርጋት የሚበቃ ስፍራ ያለው ነው:: ቤቱ ከተለያዩ የሕንፃ መሳሪያዎች የተሰራ ሊሆን ይችላል:: ማለትም ከድንጋይ፣ ከሸክላ፣ ከብሎኬት፣ ከሲሚንቶ፣ ከእንጨት፣ ወይም ከሌሎች ከአካባቢው ከተገኙ የሕንፃ መሳሪያዎች ሊሰራ ይችላለ:: ይሁን እንጂ ለዚህ ጥናት በጊዜያዊነት የሚሰሩ ቤቶች ማለትም አሰራራቸው ለጊዜያዊ መጠለያ ተብለው እንጨት በመሬት በመትከል ቋሚነት በሌለው ግድግዳ እንዲሁም በካርቶን፣ በፕላስቲክ፣ ...ወዘተ. የተሰሩትን አያጠቃልልም:: ይሁን እንጂ የከብት አርቢ (በተለምዶ ዘላን በሚባሉት) አካባቢ ቤቶች በአሰራራቸው ቋሚ ስለማይመስሉ እንደ ቤት ሳይቆጠሩ እንዳይታለፉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል::

ማሳሰቢያ:-ቤቱን በማህበር ወይም በግል በብድር ቢሰራውም በዚህ ይጠቃለላል::ይሁን እንጂ ከሌላ ቤተሰብ ጋር በሽርክና የያዛቸው መኖሪያ ቤቶች በዚህ አይጠቃለሉም::

**F. 2 How many separate rooms are there in your dwelling?**

**ረ. 2 የመኖሪያ ቤቱ ስንት ክፍሎች አሉት?**

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት የሚኖርበት መኖሪያ ቤት ስንት ክፍሎች እንዳሉት በመጠየቅ የክፍሎቹ ብዛት በተሰጡት ክርድ ኮለሞች ይሞላሉ::

ማሳሰቢያ:
1. የማብሰያ ክፍሎችና የመታጠቢያ ክፍሎች በዚህ አይካተቱም::
2. የክፍሎቹ ብዛት በሚጠየቅበት ወቅት ከዋናው ቤት ውስጥ ካሉ ክፍሎች በተጨማሪ የሰርቪስ ክፍሎችንም ያካትታል::
3. ለድርጅት የሚጠቀምባቸው ክፍሎች በዚህ አይካተቱም::

**F. 3 How many plot of land are owned by the household?**

**ረ. 3 ቤተሰቡ ምን ያህል የራሱ ማሳ/መሬት አለው?**

ከቤተሰቡ አባላት መካከል /ኃላፊውን ጨምሮ/ በጥናቱ ወቅት ምን ያህል የራሳቸው የሆነ ማሳ/መሬት እንዳላቸው ተጠይቆ ብዛቱ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይመዘገባል:: የራሱ መሬት ሲባል ከመንግሥት ወይም ከሌላ ቤተሰብ በህጋዊ መንገድ ቤተሰቡ ለእርሻ፣ ለእርባታ፣ ለግጦሽ፣ በእዳሪነት፣ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ ወዘተ ... እንዲሆን ተብሎ የተገኘ መሬት ማለት ነው::

ማሳሰቢያ:- በጥያቄ ረ. 1 ቤተሰቡ የሚኖርበት መኖሪያ ቤት የግሌ የሚል መልስ ከሰጠ ቢያንስ አንድ ቤትና ቤቱ ያረፈበት መሬት እንዳለው ማስተዋል ያስፈልጋል::

**F. 4 How does the amount of land owned compare with 1 year ago?**

**ረ. 4 ቤተሰቡ በአሁኑ ወቅት ያለው ማሳ/መሬት ብዛት ከአምናው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?**

በተራ ቁጥር ረ.3 ላይ ቤተሰቡ አሁን አለኝ ብሎ የጠቀሰው መሬት ይዞታ ከባለፈው አንድ ዓመት ጋር ሲነፃፀር ምን እንደሚመስል በመጠየቅ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት አማራጮች መካከል በመምረጥ ትክክለኛው ኮድ/ክብ ይጠቆራል::

<u>አማራጭ ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| Less now | 1 | አሁን ቀንሷል |
| Same now | 2 | ለውጥ የለውም |
| More now | 3 | አሁን ጨምሯል |
| Don't know | 4 | አላውቅም |

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት መሬት ከሌለውና ባለፈው 12 ወራት ውስጥ ምንም ዓይነት መሬት ከሌለው "ለውጥ የለውም" የሚለው አማራጭ ኮድ/ክብ ይጠቆራል፡፡

## F. 5 Does the household use land it does not own?

## ረ.5 ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ ማሳ/መሬት የሚጠቀም ከሆነ መሬቱን በምን መልኩ አገኘው?

ቤተሰቡ ወይም የቤተሰቡ አባል በጥናቱ ወቅት የራሱ ያልሆነን መሬት ለእርሻ፣ ለእርባታ፣ ለግጦሽ ወዘተ ... ይጠቀም እንደሆነ በመጠየቅ የሚጠቀም ከሆነ መሬቱ በምን መልኩ እንደገኘው በመጠየቅ ተገቢውን ኮድ/ክብ በመምረጥ ይጠቆራል፡፡ ነገር ግን ቤተሰቡ ምንም ዓይነት የሌላ ቤተሰብ መሬት የማይጠቀም ከሆነ "አልጠቀምም" የሚለው ኮድ/ክብ ይጠቆራል፡፡

<u>አማራጭ ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| No | 1 | አልጠቀምም |
| Rented | 2 | በኪራይ |
| Sharecropped | 3 | በማጋዞ/ምርትን በማካፈል/ |
| Private land provided free | 4 | ከሌላ ቤተሰብ በነፃ የተገኘ |
| Open access land | 5 | ጫካ በመመንጠር /አዲስ ማሳ በማዘጋጀት |

## F.6 How many plots of land does the household use that it does not own?

## ረ. 6 ቤተሰቡ የራሱ ያልሆነ ስንት ማሳ (መሬት) ይጠቀማል?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት በጥያቄ ረ.5 ላይ የራሱ ያልሆነ መሬት ለሥራ እጠቀማለሁ ብሎ ከኮድ 2 እስከ ኮድ 5 ካሉት ቁጥሮች ከተሞላ ምን ያህል መሬት/ማሣ በአሁኑ ወቅት በመጠቀም ላይ እንዳለ በመጠየቅ ቁጥሩ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይመዘገባል፡፡ ሆኖም ምንም ዓይነት ማሳ/መሬት ከሌለው ማለትም በጥያቄ ረ.5 ኮድ "1" ከተጠቆረ ይህ ጥያቄ ሳይጠየቅ ይታለፋል፡፡

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ቤተሰቡ በጥናቱ ዓመት ውስጥ መሬት ከሌላ ቤተሰብ በኪራይ፣ በነፃ ወይንም ደግሞ አዲስ ማሣ በመመንጠር አዘጋጅቶ የተጠቀመ ከሆነ የመሬቱ ብዛት በጥናቱ ወቅት ይመዘገባል፡፡

**F. 7 How does the amount of other land use compare with 1 year ago?**

**ረ. 7 ቤተሰቡ <u>የራሱ ያልሆነ</u> ማሳ (መሬት) የተጠቀመው ብዛት ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?**

በተራ ቁጥር ረ.6 ላይ ቤተሰቡ አሁን/በጥናቱ ወቅት የራሱ ያልሆነ መሬት እጠቀማለሁ ብሎ ያስመዘገበው መሬት ብዛት ከባለፉት 12 ወራት ጋር ሲነፃር ምን እንደሚመስል በመጠየቅ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ተመርጦ ተስማሚው ኮድ/ኮብ ይጠቆራል።

<u>አማራጭ ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| Less now | 1 | አሁን ቀንሷል |
| Same now | 2 | ተመሳሳይ ነው |
| More now | 3 | አሁን ጨምሯል |
| Don't know | 4 | አላውቅም |

<u>ማሳሰቢያ</u>:- በጥናቱ ዓመት ቤተሰቡ ምንም ዓይነት መሬት ከሌላ ቤተሰብ በኪራይ፣ በነፃ ...ወዘተ አግኝቼ አልተጠቀምኩም ብሎ በጥያቄ ረ.6 "00" ከተሞላ በዚህ ጥያቄ አማራጭ "3" ሊጠቆር አይገባም።

**F. 8 How many head of cattle are currently owned by the household?**

**ረ. 8 ቤተሰቡ ምን ያህል የቀንድ ከብቶች አሉት?**

ቤተሰቡ ወይም የቤተሰቡ አባል በአጠቃላይ ምን ያህል የቀንድ ከብቶች እንዳሉት ተጠይቆ ብዛቱ በተሰጡት የብዛት መፃፊያ ሳጥኖች ውስጥ ይመዘገባል። ቤተሰቡ ያሉት ከብቶች ብዛት ብዛታቸው ከ10 በታች ከሆነ "00" ክፍት እየተጨመረ የሚፃፍ ሲሆን 100 ካነስ ደግሞ "0" ከቁጥሩ በፊት እየተጨመረ ይፃፋል ማለት ነው። (ምሳሌ:- 008፣ 005፣ 080፣ 015፣ 018፣ 030 ...ወዘተ)

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ቤተሰቡ ያሉት የቀንድ ከብቶች ሲባል በጥናቱ ወቅት ሌላ ቤተሰብ ዘንድ የሚገኙ፣ ከቤተሰቡ ለጊዜው መኖ ፍለጋ ወደ ሌላ ቦታ የሄዱ ...ወዘተ እንደሚያካትት ማስተዋል ያስፈልጋል።

**F. 9 How does this number of cattle compare to the number one year ago?**

**ረ. 9 አሁን ያሉት የቀንድ ከብቶች ብዛት ከባለፈው ዓመት ጋር ሲወዳደር ምን ይመስላል?**

በጥናቱ ወቅት ቤተሰቡ ያሉት የቀንድ ከብቶች ብዛት ባለፈው 12 ወራት ውስጥ ካሉት ጋር ሲነፃፀር ምን እንደሚመስል በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛውን ኮድ በመምረጥ ይጠቆራል።

አማራጭ ኮዶች

| | | |
|---|---|---|
| Less now | 1 | አሁን ቀንሷል |
| Same now | 2 | ተመሳሳይ ነው |
| More now | 3 | አሁን ጨምሯል |
| Don't know | 4 | አላውቅም |

ማሳሰቢያ:- በጥናቱ ወቅት ቤተሰቡ ምን ያህል የቀንድ ከብቶች እንዳሉት ተጠይቆ በጥያቄ ሬ.8 "00" ከተሞላ በዚህ ጥያቄ አማራጭ "3" ሊጠቆር አይገባም።

**F.10 How many sheep and goats are currently owned by the household?**

ሬ.10 ቤተሰቡ ምን ያህል በግና ፍየሎች አሉት?

ይህ ጥያቄ በተራ ቁጥር ሬ.8 ላይ ከተጠቀሰው ጥያቄ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን በዚህ ጥያቄ ቤተሰቡ ያሉት በጎች ወይም ፍየሎች ብዛት ተጠይቆ ብዛቱ በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይሞላል።

ማሳሰቢያ:- አሳማ ያላቸው ቤተሰቦች ከተገኙ የአሳማዎቹ ብዛት በዚህ ክፍል ውስጥ ብዛታቸው ይታያል።

**F.11 How does the number of goats and sheep compare to the number of one year ago?**

ሬ.11 ቤተሰቡ ያሉት በግና ፍየሎች ብዛት ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

በተራ ቁጥር ሬ.10 ቤተሰቡ ያስመዘገባቸው የበጎችና የፍየሎች/አሳማዎች ብዛት ከባለፈው 12 ወራት ውስጥ ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ምን እንደሚመስል በመጠየቅ ጨምሮ ከሆነ "አሁን ጨምሯል" የሚለውን ይጠቆራል ቀንሶ ከሆነ ደግሞ "አሁን ቀንሷል" የሚለው ኮድ ይጠቆሯል።

**F.12 How many poultry are currently owned by the household?**

ሬ.12 ቤተሰቡ ምን ያህል ዶሮዎች አሉት?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ምን ያህል ለእርባታ ወይም/እና ለስጋ የሚውሉ ዶሮዎች እና የዶሮ ዝርያ ያላቸው እንደ ዳክዬ፣ ዝይ/ጊዚ/፣ ተርኪ እና የመሳሰሉት ምን ያህል እንዳለው ተጠይቆ ብዛታቸው በተሰጡት ካርድ ኮለሞች ውስጥ ይመዘገባሉ። ብዛታቸው ከ10 በታች ከሆነ "00" ከፍት እየተጨመረ የሚፃፍ ሲሆን 100 ካነሰ ደግሞ "0" ከቁጥሩ በፊት እየተጨመረ ይፃፋል ማለት ነው። (ምሳሌ:- 008፣ 005፣ 080፣ 015፣ 018፣ 030 ...ወዘተ)

**F.13 How does this number of poultry compare to the number of one year ago?**

**ረ.13 አሁን ያሉት የዶሮዎች ብዛት ባለፈው ዓመት ከነበሩት ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?**

በዚህ ክፍል ቤተሰቡ በተራ ቁጥር ረ.12 አሁን አሉኝ ብሎ ያስመዘገበው የዶሮዎች ብዛት ባለፈው 12 ወራት ከነበሩት ጋር አነፃፅሮ በአሁኑ ወቅት ያሉት የዶሮዎች ከባለፈው 12 ወራት ጋር ሲነፃፀር ቀንሶ ከሆነ "Less now" በሚለው ትይዩ ያለው ኮድ/ክብ ይጠቆራል:: ጨምሮ ከሆነ ደግሞ "More now" በሚለው ትይዩ ያለው ኮድ/ክብ የሚጠቆር ሲሆን ለውጥ ከሌለው ደግሞ "Same now" በሚለው ትይዩ ያለው ኮድ/ክብ ይጠቆራል::

**F.14 How many of the following does the household own?**

**ረ.14 ቤተሰቡ ምን ያህል ______ አለው?**

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት የተዘረዘሩትን እያንዳንዱን ንብረት አስመልክቶ ያለው መሆኑና አለመሆኑን ይጠየቃል:: ለእያንዳንዱ የተዘረዘረ ንብረት ቤተሰቡ ተጠይቆ አለኝ የሚል ከሆነ ብዛቱን በመጠየቅ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይሞላል::

<u>ማሳሰቢያ:-</u>

1. ቤተሰቡ በእያንዳንዱ ንብረት ስር ያለው ብዛት 8 እና ከዚያ በላይ ከሆነ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ "8" ይሞላል:: ነገር ግን ጥያቄው የማያስፈልገው ወይም የማይመለከተው ከሆነ ደግሞ "9" በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይሞላል::

2. እያንዳንዱ ቤተሰብ አሉኝ ብሎ የሚያስመዘግበውን ንብረት በጥናቱ ወቅት አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ንብረት መሆን ይኖርበታል::

**F.15 How many times in the past week did you have electric power interruptions for more than one hour?**

**ረ.15 ባለፈው ሳምንት ምን ያህል ጊዜ ከአንድ ሰዓት የበለጠ መብራት መቋረጥ አጋጠመዎት?**

ቤተሰቡ እየተጠቀመበት የሚገኘውን የኤሌክትሪክ መብራት ባለፈው አንድ ሳምንት ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ከ1 ሰዓት በላይ የኤሌክትሪክ መቋረጥ አጋጥሞ እንደሆነ በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በትይዩ የተሰጠውን ኮድ/ክብ ይጠቆራል::

<u>አማራጭ ምክንያቶችና ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| **Household does not have electricity** | 1 | ቤተሰቡ መብራት የለውም |
| **No power interruptions** | 2 | ምንም ዓይነት የመብራት መቋረጥ አላጋጠመም |
| **Once** | 3 | አንድ ጊዜ ብቻ |
| **Two times** | 4 | ሁለት ጊዜ ብቻ |
| **More than 2 times** | 5 | ከሁለት ጊዜ በላይ |

**F.16 How many months in the last year did you have problems satisfying the food needs of the household?**

ረ.16 ባለፈው ዓመት የቤተሰቡን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት የምን ያህል ወራት ችግር አጋጥሟል?

በባለፈው ዓመት የምርት ዘመን ወቅት ያመረተው ምርት ቤተሰቡ የ1995 ዓ.ም. ምርት እስከሚመረት ድረስ ምን ያህል ወራት የምግብ እጥረት አጋጥሞት እንደሚሆን በመጠየቅ የወራቱን ብዛት በተሰጠው ሳጥኖች ውስጥ ይፃፋል:: ቤተሰቡ ሰብል አምራች ካልሆነ የሚያገኘው ገቢ ከገምት ውስጥ በማስገባት በዓመቱ ውስጥ ለምን ያህል ወራት ችግር እንዳጋጠመው ተጠይቆ በተሰጠው ሳጥኖች ውስጥ ይሞላሉ::

<u>ምሳሌ:-</u> በ1994 ዓ.ም. የምርት ዘመን ያመረተው ምርት ቤተሰቡን ለ8 ወራት መግቧል እንበል የ1995 ዓ.ም. ምርት እስከሚደርስበት ጊዜ ድረስ የ4 ወር የምግብ እጥረት ቢያጋጥመው "04" በተሰጠው ሳጥኖች ውስጥ ይሞላሉ ማለት ነው::

**F.17 How do you compare overall economic situation of the HOUSEHOLD with one year ago?**

ረ.17 በአሁኑ ወቅት <u>*የቤተሰቡ አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ*</u> ከባለፈው 12 ወርት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ያለውን አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ከባለፈው ዓመት "ከባለፈው 12 ወራቶች" ጋር በማነፃፀር በአሁኑ ወቅት ኑሮ ምን እንደሚመስል ተጠይቆ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ ከምክንያቱ ፊት ለፊት የሚገኘውን ኮድ/ክብ ይጠቆራል::

<u>አማራጭ ምክንያቶች ኮድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| Much worse now | 1 | በጣም ብሶብኛል |
| A little worse now | 2 | በመጠኑ ቀንሷል |
| Same | 3 | ለውጥ የለውም |
| A little better now | 4 | መጠኑ አሁን ተሻሏል |
| Much better now | 5 | በጣም ተሻሽሏል |
| Don't know | 6 | ማወዳደር አልችልም |

**F.18 How do you compare overall economic situation of the COMMUNITY with one year ago?**

ረ.18 በአሁኑ ወቅት <u>የአካባቢው ማህበረሰብ</u> አጠቃላይ የኑሮ ሁኔታ ባለፈው አንድ ዓመት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል?

የተመረጠው የቤተሰቡ አካባቢ ያለው ሕብረተሰብ አባላት የኑሮ ሁኔታ በአጠቃላይ ምን እንደሚመስል በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጭ ምክንያቶች ፊት ለፊት ክብ ይጠቆራል። የተጠቀሱት ምክንያቶች በተራ ቁጥር ረ.17 ካለው ጋር ተመሳሳይነት ሲሆን አማራጭ ምክንያቶቹና ኮዱ ከገፁ____ ተመልከት/ተመልከቺ።

**F.19 If the household needed 100 Birr for an emergency could the household obtain it within a week?**

ረ.19 ቤተሰቡ አንድ አስቸኳይ ችግር/አደጋ ቢያጋጥመውና 100 ብር ቢያስፈልገው በአንድ ሳምንት ውስጥ ማግኘት ይችላልን?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ቢያጋጥመው በአንድ ሣምንት ውስጥ 100 ብር ማግኘት ይችል ወይም አይችል እንደሆነ በመጠየቅ እችላለሁ ካለ አዎን "yes" በሚለው አንፃር ያለውን "Y" የሚለውን ክብ የሚጠቆር ሲሆን 100 ብር በሳምንት ማግኘት አልችልም ካለ ደግሞ የለም "No" በሚለው አንፃር የሚገኘው "N" የሚለው ክብ ይጠቆራል።

**F.20 How would the household obtain the 100 Birr?**

ረ.20 ቤተሰቡ በሳምንት 100 ብር ማግኘት ከቻለ ምንጩ ምንድን ነው?

በተራ ቁጥር ረ.19 ቤተሰቡ ያልተጠበቀ ችግር ቢገጥመኝ 100 ብር በአንድ ሣምንት ውስጥ ማግኘት እችላለሁ ካለ ከየት ማግኘት እንደሚችል በመጠየቅ ከ1-7 ካሉት የገቢ ምንጭ ዝርዝሮች መካከል ዋነኛው ምክንያት በመምረጥ ከምክንያቱ ትይዩ ያለው ኮድ/ክብ ይጠቆራል።

<u>ዋና ዋና የገቢ ምንጮች እና ኮድ</u>

| | | |
|---|---|---|
| Sale of animal | 1 | የእንስሳት ሽያጭ |
| Sale of other farm/ business | 2 | ከሌላ የእርሻ ምርት ሽያጭ/ ከንግድ |
| Sale of household asset | 3 | ቋሚ ንብረት በመሸጥ |
| Owns cash | 4 | ከተቀማጭ ገንዘብ |
| Saving association (Eqib, Edir) | 5 | ቁጠባ ማኅበር፣ ዕድር፣ ዕቁብ |
| Loan | 6 | ብድር |
| Other | 7 | ሌላ |

## *Section G: Household Amenities*

## *ክፍል ቀ የቤተሰቡ ስለሚጠቀምባቸው ግልጋሎቶች*

**G.1: What is the material of the roof of the house?**

ቀ.1: የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው የተሰራው ከምንድን ነው?

ቤተሰቡ አሁን የሚኖርበትን ቤት የቤቱ ጣሪያ በአብዛኛው ከምን እንደተሰራ ተጠይቆ ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ተስማሚውን በመምረጥ በትይዩ የሚገኘውን ኮድ/ኮብ ይጠቅራል።

<u>አማራጭ ምክንያቶችና ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| Corregated iron sheet | 1 | ቆርቆሮ |
| Thatch or grass | 2 | ከሰንበሌጥ/ሳር |
| Wood and mud | 3 | ከእንጨትና ከጭቃ |
| Reed and Bambo | 4 | ከቀርከሃ/ሸንበቆ |
| Other | 5 | ሌላ |

**G.2: What is the material of the walls of the house?**

ቀ.2: የቤቱ ግድግዳ በአብዛኛው የተሰራው ከምንድን ነው?

ቤተሰቡ አሁን የሚኖርበትን ቤት የቤቱ ግድግዳ <u>በአብዛኛው</u> ከምን እንደተሰራ ተጠይቆ ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ተስማሚውን በመምረጥ በትይዩ የሚመለከተው ኮድ/ኮብ ይጠቅራል።

አማራጭ ምክንያቶችና ኮዶች

| | | |
|---|---|---|
| Wood and mud | 1 | ከእንጨትና ከጭቃ |
| Wood and thatch | 2 | ከእንጨትና ሰንበሌጥ |
| Reed/bambo | 3 | ቀርቀሃ/ሸንበቆ |
| Stone and mud | 4 | ጭቃና ድንጋይ |
| Stone and cement | 5 | ሲሚንቶና ድንጋይ |
| Blocket | 6 | ብሎኬት |
| Bricks | 7 | ሸክላ/ጡብ |
| Others | 8 | ከሌሎች |

**G.3: What is the main source of drinking water?**

ቀ.3: ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የሚያገኘው ከየት ነው ?

ቤተሰቡ በጥናቱ ወቅት የመጠጥ ውኃ የሚያገኘው ከየት እንደሆነ በመጠየቅ የተሰጠውን መልስ ከተዘረዘሩት አማራጮች ጋር በማዛመድ ተገቢውን መልስ በትይዩ የተሰጠውን ኮድ/ኮብ ይጠቅራል።

ቤተሰቡ ለመጠጥ የሚሆን ውኃ የሚያገኘው

| | | |
|---|---|---|
| Tape inside the house | 1 | ከቤት ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ |
| Tape in the compound /Private/ | 2 | ከግቢ ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ/የግል |
| Tape in the compound /Shared/ | 3 | ከግቢ ውስጥ ካለ የቧንቧ ውኃ/የጋራ |
| Tape outside the compound /Shared/ | 4 | ከግቢ ውጭ ካለ የቧንቧ ውኃ/የጋራ |
| Protected well/spring | 5 | ከተጠበቀ የጉድጓድ /ምንጭ ውኃ |
| Unprotected well/spring | 6 | ካልተጠበቀ የጉድጓድ/ምንጭ ውኃ |
| River, lake or pound | 7 | ከወንዝ፣ ሐይቅ፣ ኩሬ፣ ...ወዘተ. |

<u>የተጠበቀ ጉድጓድ ወይም ምንጭ</u>

1. በጉድጓዱ ወይም በምንጩ ዙሪያ በሲሚንቶ የተገነባ ግንብ መኖር አለበት። ይኸውም:-

ሀ. ጉድጓድ ከሆነ ጉድጓዱ በሚገኝበት የአፈር ሁኔታ መሠረት ግንቡ ቢያንስ ከ2 እስከ 4 ሜትር ወደ መሬት ውስጥ የገባ እና 70 ሳንቲ ሜትር ያህል ደግሞ ከመሬት ወደ ላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል።

ለ. ምንጭ ከሆነ ግንቡ ጠንካራ መሬት ወይም አለት እስከሚገኝበት ድረስ መሬት ውስጥ የገባና እንደ አስፈላጊነቱ ከመሬት በላይ ከፍ ብሎ የወጣ መሆን ይኖርበታል። ግንቡ በአንድ በኩል ውኃ ማውጫ ክፍት ቧንቧ ያለው መሆን አለበት።

2. በጉድጓድም ሆነ በምንጭ ዙሪያ የተገነባው ግንብ ከላይ ከሲሚንቶ የተሰራ ወይም ሌላ ዓይነት ጥብቅ ክዳን እንዲኖረው ያስፈልጋል።

3. ወደ ጉድጓዱ ወይም ምንጩ ጎርፍ እንዳይገባ የጎርፉን አቅጣጫ የሚቀይር ተስማሚ ቦይ ጎርፍ ሊመጣ ከሚችልበት አካባቢ ወይም አቅጣጫ መኖር አለበት።

4. እንደ መጸዳጃ ቤት ከመሳሰሉት ውኃውን ሊበክሉ ከሚችሉ ነገሮች ጉድጓዱም ሆነ ምንጩ ቢያንስ ቢያንስ ከ25 እስከ 30 ሜትር የራቀ መሆን አለበት።

5. በተራ ቁጥር 4 የተገለፀው በካይ ቆሻሻ ዓይነት የውኃው ጉድጓድ ወይም ምንጩ ከሚገኝበት ከፍ ባለ ቦታ ቢኖር ርቀቱ በተራ ቁጥር 4 ላይ ከተጠቀሰው ርቀት ብዙ መብለጥ ይኖርበታል።

ስለዚህ ቤተሰቡ ውኃ የሚያገኘው ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በሚያሟላ ሁኔታ ከተጠበቀ ጉድጓድ ወይም ምንጭ ከሆነ ከተጠበቀ ውኃ እንደተጠቀመ ይቆጠራል፣ በቧንቧ የሚመጣ ውኃ ካልሆነ በስተቀር ከወንዝ ወይም ከሐይቅ እየተቀዳ የሚገኘው ውኃ በአጠቃላይ ያልተጠበቀ ነው ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ከወንዝ፣ ከሐይቅ ወይም ከኩሬ እየቀዳ የሚጠቀም ቤተሰብ በተጠበቀ ውኃ አይጠቀምም ማለት ነው። ከቧንቧ የሚገኝ ውኃ ግን በአጠቃላይ እንደተጠበቀ ይቆጠራል። ውኃው ግን ወደ ተጠቃሚዎቹ ቤት የሚያደርሰው በሰው ጉልበት ወይም በጋማ ከብቶች ሊሆን ይችላል።

**G.4: What kind of toilet facility does your household use?**

ቀ.4: ቤተሰቡ የሚጠቀምበት በዋነኛ የመፀዳጃ ዓይነት ምንድን ነው?

ቤተሰቡ በዋነኝነት የሚጠቀምበት መፀዳጃ ምን እንደሆነ ከተሰጡት አማራጮች <u>በዋነኛነት</u> የሚጠቀምበት የመፀዳጃ ዓይነት ተጠይቆ ተገቢው ኮድ/ኮብ ይጠቆራል::

አማራጭ ምክንያቶችና ኮዶች

| | | |
|---|---|---|
| Private flush toilet | 1 | በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ/የግል |
| Shared flush toilet | 2 | በውኃ የሚወርድ መፀዳጃ/የጋራ |
| Private pit lafrine | 3 | የጉድጓድ መፀዳጃ/የግል |
| Share pit latrine | 4 | የጉድጓድ መፀዳጃ/የጋራ |
| Household container | 5 | ባልዲ/ፖፖ |
| Field /forest | 6 | ሜዳ /ጫካ |
| Other | 7 | ሌላ |

## G.5: What is the main fuel used for cooking?

ቀ.5: ቤተሰቡ በዋነኛነት የሚጠቀምበት የማገዶ ዓይነት ምንድን ነው?

ቤተሰቡ ከተዘረዘሩት አማራጮች ውስጥ <u>በዋነኛነት</u> የሚጠቀመው የማገዶ ዓይነት ተጠይቆ ተገቢው ኮድ/ኮብ ይጠቆራል::

አማራጭ ምክንያቶችና ኮዶች

| | | |
|---|---|---|
| Mainly collected firewood | 1 | የተሰበሰበ እንጨት |
| Mainly purchased firewood | 2 | የተገዛ እንጨት |
| Charcoal | 3 | ከሰል |
| Kerosene | 4 | ነጭ ጋዝ |
| Butane gas | 5 | ቡታ ጋዝ/የሲሊንደር |
| Electricity | 6 | ኤሌክትሪክ |
| Leaves, dung, caker etc | 7 | ቅጠል/ኩበት/ስጋቱራ |
| Others | 8 | ሌላ |

**G 6: What is the main fuel used for lighting?**

ቀ .6: ቤተሰቡ ለቤቱ በዋነኛነት የሚጠቀመው የመብራት ዓይነት ምንድን ነው?

የቤተሰቡ <u>በዋነኛነት/በአብዛኛው</u> የሚጠቀመው የመብራት ዓይነት ተጠይቆ ከተዘረዘሩት አማራጮች እንዱንና ዋናውን በመምረጥ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ በትይዩው የተሰጠውን አማራጭ ኮድ/ኮብ ይጠቆራል::

አማራጭ ምክንያቶችና ኮዶች

| | | |
|---|---|---|
| Kerosene | 1 | ኩራዝ/ፋኖስ |
| Private electricity | 2 | ኤሌክትሪክ/ቆጣሪ/በግል |
| Shared electricity | 3 | ኤሌክትሪክ/ቆጣሪ/በጋራ |
| Firewood | 4 | ማገዶ /እንጨት፣ ቅጠል፣ አገዳ ...ወዘተ./ |
| Candles | 5 | ሻማ/ጧፍ |
| Other | 6 | ሌላ |

**G 7: How far it from here to reach the nearest ________?**

**ቀ. 7: ቅርብ ያለው አገልግሎት ሰጪ ተቋም በምን ያህል ርቀት ላይ ይገኛል?**

ቤተሰቡ ከሚገኝበት መኖሪያ ቤት አንስቶ ቅርብ የሆነውን አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ እስከሚገኝበት ድረስ ምን ያህል እርቀት እንዳለው "በኪ.ሜትርና በሰዓት" በመጠየቅ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይሞላል።

<u>ማስታወሻ:</u>

- ቤተሰቡ የአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ርቀቱን <u>በሰዓት ብቻ</u> የሚያውቅ ከሆነ ምን ያህል ሰዓትና ደቂቃ እንደሚጓዝ የሚመዘገብ ሲሆን በኪ.ሜትር መመዝገቢያ ሳጥን ላይ "99" ይመዘገባል።

- ሆኖም <u>ርቀቱን በኪ.ሜትር</u> ብቻ ከተናገረ ለሰዓትና ደቂቃ መፃፊያ በተሰጠው ቦታ ላይ "9999" በመሙላት ርቀቱ በኪ.ሜትር ብቻ ይመዘገባል።

- ቤተሰቡ የአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ ርቀቱን <u>በሰዓትና በኪ.ሜትር</u> መናገር የሚችል ከሆነ ሰዓትና ደቂቃ በሚለው አንፃር እና ኪ.ሜትር በሚለው አንፃር ርቀቱ ይመዘገባል።

<u>ማሳሰቢያ</u>

1. ርቀቱ በኪ.ሜትር ከ97 ከበለጠ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ "97" ይሞላል።
2. በቅርብ ያለው ተቋም የመንግስት፣ የግለሰብ ወይም የግብረ-ሰናይ ድርጅት ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ተገቢ ነው።

## Section H: Welfare

## ክፍል በ: ኢኮኖሚና ማህበራዊ ደህንነት

ይህ ክፍል የሚመለከተው የቤተሰቡን አባላት አንድ በአንድ በመጠየቅ ሳይሆን ስለቤተሰቡ አጠቃላይ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

**H.1: Has the household experienced any of the following shocks in the last 12 months which seriously affected its wealth position?**

**በ.1: ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት የኑሮ ሁኔታ የሚያናጋ አደጋ/ችግር ደርሶበት/አጋጥሞት ነበርን?**

<u>የአደጋ/ችግር ዓይነቶችና ኮዳቸው</u>

| | | |
|---|---|---|
| Death | 1 | ሞት |
| Major illness | 2 | ከፍተኛ ህመም/በሽታ |
| Loss of job | 3 | ከሥራ መፈናቀል/መሰናበት |
| Drought | 4 | ድርቅ/ረሃብ |
| Flood | 5 | ጎርፍ |
| Major plot damage | 6 | ከፍተኛ የሆነ የሰብል መውደም |
| Death of animas | 7 | የቤት እንስሳት ሞት |

ቤተሰቡን ባለፈው 12 ወራቶች ውስጥ የኑሮ ሁኔታውን የሚያናጋ አደጋ/ችግር ማለትም ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 ካሉት ውስጥ አጋጥሞት ከሆነ እያንዳንዱን የተዘረዘሩትን አደጋዎች/ችግሮች በመጠየቅ አደጋ/ችግር አጋጥሞኝ ነበር ካለ በጥያቄ "ሀ" አዎን (Yes) የሚለውን ክብ በደረሰበት አደጋ አንፃር የሚጥቆር ሲሆን አደጋ ካልደረሰበት ግን "የለም" (No) የሚለውን ክብ ይጠቆራል።

ጥያቄ "ለ" የሚመለከተው ደግሞ በጥያቄ "ሀ" ቤተሰቡ የኑሮ ሁኔታዬን የሚያናጋ አደጋ/ችግር አጋጥሞኝ ነበር ብሎ በአደጋዎች አንፃር አዎን "Yes" ለተጠቆረባቸው አደጋዎች ሲሆን ለእነዚህ አደጋዎች መፍትሄ መስጠቱን ወይም አለመስጠቱን የሚጠየቅ ስለሆነ መፍትሄ <u>**ለአደጋዎቹ ካልሰጠ**</u> በዚህ ጥያቄ ስር ያለው ክብ ይጠቆርና ጥያቄው ያበቃል። ሆኖም ለደረሰበት አደጋ/ችግር መፍትሄ ከሰጠ በጥያቄ "ለ" ስር ያለው ክብ <u>**ሳይጠቆር ይታለፍና**</u> ላጋጠመው አደጋ መፍትሄ የሰጠው ምን በማድረግ እንደሆነ ከዚህ በታች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ጋር በማገናዘብ ተስማሚውን አማራጭ ማጥቆር ያስፈልጋል። <u>በዚህን ጊዜ ለአንድ አደጋ/ችግር ቤተሰቡ የሰጠው መፍትሄ ከአንድ በላይ ሊሆን እንደሚችል ማስተዋል ያስፈልጋል።</u>

<u>አማራጭ መልሶችም</u>

| | | |
|---|---|---|
| Food aid | 1 | የምግብ ዕርዳታ |
| Sales of animals | 2 | የቤት እንስሳት በመሸጥ |
| Sales of other farm assets | 3 | ሌሎች የእርሻ መገልገያዎችን በመሸጥ |
| sales of household assets | 4 | የቤት ዕቃዎች በመሸጥ |
| Own cash | 5 | ካለኝ ጥሬ ገንዘብ |
| Equb | 6 | በዕቁብ |
| Edir | 7 | በዕድር |
| Loan | 8 | በብድር |
| gift | 9 | በስጦታ |
| Other | 10 | ሌላ |

<u>ምሣሌ</u>:- አንድ ገበሬ የእርሻ ሰብሉን በረዶ ቢመታበት ነገር ግን ቤተሰቡ ይህ ሰብል በበረዶ በመመታቱ ምክንያት ምንም አይነት የኑሮ መናጋት/ችግር ካላጋጠመው በጥያቄ "ሀ" "የሰብል መውደም" በሚለው ትይዩ "N" የሚለው ኮብ ይጠቆራል ማለት ነው።።

## Section I: Children Under 5

## ክፍል ተ: እድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት

ይህ ክፍል የሚመለከተው እድሜአቸው ከ5 ዓመት በታች (ከ"60" ወራት በታች) የሆኑትን ሕፃናት ብቻ ነው:: በመሆኑም በክፍል ለ ጥያቄ ቁጥር ለ.5 ዕድሜያቸው በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ከ5 ዓመት በታች ከሆነ ማለትም "05" በታች ቁጥር በሳጥኑ ውስጥ ከታየ በዚህ ክፍል ስለሕፃኑ አስፈላጊው መረጃ ይሞላል::

> **I.1: For each child under 5 enter the child and mother's number from the list of household members. Enter "00" if the child's mother is deceased or is not a member of household.**
>
> **ተ.1: ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህፃናት የህፃኑንና የእናቱን መለያ ቁጥር ከቤተሰብ አባላት ዝርዝር ተወስዶ ይሞላል:: እናቱ የቤተሰብ አባል ሳልሆነችና በሕይወት ለሌለች "00" መሞላት አለበት::**

<u>የሕፃኑ ተራ ቁጥር</u>

በዚህ ጥያቄ የሚመዘገበው ከ"ክፍል ለ" (member of household number /የቤተሰቡ አባላት ተራ ቁጥር) መመዝገቢያ ላይ ከተሰጠው ተራ ቁጥር ሲሆን ዕድሜያቸው 5 ዓመት እና በታች ለሆኑ ህፃናት ብቻ የሕፃኑ ተራ ቁጥር በቀጥታ በማስተላለፍ ህፃን /Child/ በሚለው ስር ይሞላል:: ሕፃናት ሲመዘገቡ ተከታታይ ባለው መንገድ ሳይሆን ስለሚችል የሕፃኑ ተራ ቁጥር ሲተላለፍም በ"ክፍል ለ" የተመዘገበውን ተራ ቁጥር ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት እንዳለ ነው::

> <u>ለምሳሌ</u>:- በ"ክፍል ለ" ለሕፃኑ የተሰጠው ተራ ቁጥር "06" ቢሆን በዚህ ቅፅ ህፃን /Child/ በሚለው ስር ባሉት ሳጥኖች ውስጥ ለሕፃኑ የሚሰጠው ተራ ቁጥር "06" ይሆናል ማለት ነው::

<u>የሕፃኑ ወላጅ እናት ተራ ቁጥር</u>

በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሕፃን ወላጅ እናት መጀመሪያ የቤተሰቡ አባል መሆን አለመሆኗን በመጠየቅ መልሱ "አዎን" ከሆነ ከ"ክፍል ለ" (member of household number/የቤተሰቡ አባላት ተራ ቁጥር) መመዝገቢያ ላይ ከተሰጠው ተራ ቁጥር ከተዘረዘሩት መካከል ለሕፃኑ ወላጅ እናት የተሰጠውን ተራ ቁጥር ምንም ዓይነት ማስተካከያ ሳይደረግበት ወደዚህ ክፍል እናት/mother/ በሚለው ሥር ባሉት ሳጥኖች ውስጥ ይሞላል:: የሕፃኑ እናት የቤተሰብ አባል ካልሆነች በሳጥኖቹ ውስጥ "00" ይፃፍ::

**I.2: Enter the child date of birth.**

**ተ.2: የህፃኑ የትውልድ ጊዜ መቼ ነው?**

ዕድሜው ከ5 ዓመት በታች የሆነው ህፃን የተወለደበት ቀን፣ ወርና ዓመተ ምህረት መቼ እንደሆነ እናቱን በመጠየቅ ለቀን፣ ለወር እና ለዓመት መሃፊያ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይመዘገባል:: <u>የህፃኑን ዕድሜን በትክክል እንዲናገሩ አስፈላጊውን የማውጣጣት ጥያቄ መጠየቅ መረጃውን ለማግኘት መሞከር አለበት::</u>

<u>ምሳሌ:</u>- ህፃኑ የተወለደው የህዳር ሚካኤል በ1991 ዓ.ም. ነው ቢባል የህፃኑ ዕድሜ ለቀን መፃፊያ በተሰጠው ሳጥን ውስጥ "12"፣ ለወር መፃፊያ በተሰጠው ውስጥ "03" እና ለዓመት በተሰጠው ሳጥን ውስጥ "91" ይሞላል::

<u>ማሳሰቢያ:</u>- የህፃኑ ዕድሜ በሚጠየቅበት ወቅት የትውልድ ቀኑና ወሩ ካልታወቀ "00" በተሰጠው ሳጥን ውስጥ ይሞላል::

**I.3: Where was the child delivered?**

**ተ.3: ህፃኑ የት ተወለደ?**

ዕድሜው ከ5 ዓመት በታች የሆነው ህፃን የት እንደተወለደ እናቱን ወይም አሳዳጊውን በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛው በመምረጥ አስፈላጊው ኮድ/ክብ ይጠቆራል:: ሆኖም ህፃኑ የተወለደው በጤና ተቋማት ወይም በቤት ውስጥ ካልሆነ "ሌላ" የሚለው አማራጭ ኮድ ይጠቆራል::

<u>የህፃኑ የመወለጃ ቦታዎች እና ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| Hospital/maternity | 1 | ሆስፒታል |
| Health clinic | 2 | ክሊኒክ |
| Health Center | 3 | ጤና ጣቢያ |
| Health Post | 4 | ጤና ኬላ |
| At home | 5 | በቤት ውስጥ |
| Other | 6 | ሌላ ቦታ |

**I.4: Who delivered the child?**

**ተ.4: ህፃኑን ማን አዋለደው?**

ህፃኑን ማን እንዳዋለደው እናቱን/አሳዳጊውን በመጠየቅ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ኮድ/ክብ ይጠቆራል

<u>አማራጭ ኮዶች</u>

| | | |
|---|---|---|
| Medical Personnel | 1 | የጤና ባለሙያ |
| Midwife | 2 | አዋላጅ ነርስ |
| Trained T.B.A | 3 | የሰለጠነ የልምድ አዋላጅ |
| T.B.A | 4 | የልምድ አዋላጅ |
| Other/self | 5 | ሌላ/እናት ራሷ |

**I.5: Record each child's weight (kg with one decimal, e.g. 4.6 kg and height (cm with one decimal, e.g. 51.3cm)**

**ተ.5: የህፃኑን ክብደት በኪ.ግራም እና የህፃኑን ቁመት በሳ.ሜትር ይሞላል::**

ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆናቸው ማለትም በሰኔ ወር 1990 ዓ.ም ወይም ከዚያ ወዲህ የተወለዱ ሁሉንም ሕፃናት መመዘንና መለካት ይኖርባቸዋል:: የሕፃናት ክብደትና ቁመት ልኬቶች በዚህ ክፍል ጥያቄ ተ.5 በታች በተሰጡት ሳጥኖች ውስጥ ይመዘገባሉ:: ቁመትና ክብደት ልኬቶች (አንትሮፖሜትሪክ ልኬቶች) ራሱን የቻለና የቤተሰብ መጠይቁ ሲጠናቀቅ የሚከናወን ተግባር ነው:: ለበለጠ ማብራሪያ ከመረጃ ሰብሳቢዎች መመሪያ መጨረሻ ላይ ከገፅ 71 እስከ 80 ያለውን ይመልከቱ::

**I.6: Did the child participate in the following?**

**ተ.6: ሕፃኑ/ሕፃኗ በሚከተሉት ፕሮግራም ተሳታፊ ነበርን?**

ህፃኑ የገንቢ ምግብ (Nutrition) ፕሮግራም ተሳታፊ ሆኖ እንደሆነ እናቱን ወይም አሳዳጊውን በመጠየቅ ተሳታፊ ሆኖ ከነበረ "Y" የሚለው ክብ የሚጠቆር ሲሆን ተሳታፊ ካልነበረ ደግሞ "N" የሚለው ክብ ይጠቆራል::

በተመሳሳይ መልኩ ሕፃኑ የክብደት ክትትል (weight-ins) ፕሮግራም ተከታትሎ እንደሆነ በመጠየቅ ተከታትሎ ከነበረ "Y" የሚለው የሚጠቆር ሲሆን ተከታትሎ የማያውቅ ከነበረ ደግሞ "N" የሚለው ክብ ይጠቆራል::

**I.7: Has child been vaccinated againest________?**

**ተ.7: ሕፃኑ የ____ ክትባት ወስዷል?**

ህፃኑ የ Measels፡ **BCG, DPT1, DPT2, DPT3, Polio0, Polio1, Polio2, Polio3, Vitamin A** ክትባት ወስዶ/ዳ እንደሆን እናቱን/አሳዳጊውን በመጠየቅ ሕፃኑ____ ክትባት ወስዶ/ዳ ከሆነ "Y" የሚለው ክብ የሚጠቆር ሲሆን ክትባቱን ካልወሰደ ደግሞ "N" የሚለው ክብ ይጠቆራል:: በዚህ ጥያቄ ውስጥ ያሉት የክትባት ዓይነቶች በተናጠል ተጠይቀው አስፈላጊው መልስ በእያንዳንዱ ክትባት ዓይነት "Y" የሚለው ወይም "N" የሚለው ክብ/ኮድ መጠቆር ይኖርበታል::

<u>ሕፃኑ የኩፍኝ (ወተቴ) Measels/ ክትባት ወስዷል?</u>

ይህ በተለይ ሕፃናትን ስለሚያጠቃው ኩፍኝ ስለሚባለው በሽታ መከላከያ ክትባት መስጠቱን ወይም አለመስጠቱን የሚገልጽ መረጃ ነው:: ክትባቱ ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ነው:: ሕፃኑ የኩፍኝ / Measels/ ክትባት ወስዶ ከሆነ የክትባቱን ካርድ በማየት አረጋግጦ ወይም ተጠይቆ የተሰጠው ምላሽ "አዎን" የሚለው ከሆነ ኮድ 1 ይጠቆራል፡ "የለም" የሚለው ከሆነ ኮድ 2

ይጠቀራ፡፡ የኩፍኝ በሽታ በአንዳንድ የሀገሪችን ክፍሎች ወተቴ ተብሎ እንደሚጠራ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

ማሳሰቢያ፡- የኩፍኝ ክትባት የሚሰጠው በክንድ ላይ ሲሆን ምንም ዓይነት ምልክት/ጠባሳ አያስቀርም፡፡

## ሕፃኑ የሳንባ ነቀርሳ (BCG) ክትባት ወስዷል?

ለሳንባ ነቀርሳ መከላከያ /Anti-Tuberculosis/ የሚሆን ክትባት አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ክትባት ነው፡፡ ሕፃኑ የቢ.ሲ.ጂ /BCG/ ክትባት ወስዶ ከሆነ ተጠይቆ ወይም የክትባት ካርዱን በማየት "አዎን" የሚለው ከሆነ ኮድ 1 ይጠቀራል፣ "የለም" የሚለው ካልወሰዱ ደግሞ ኮድ 2 ይጠቀራል፡፡

ማስታወሻ፡- የሳንባ ነቀርሳ ክትባት በግራ ትከሻ ላይ የሚሰጥ ሲሆን በግልጽ የሚታይ ጠባሳየሚተው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## ሕፃኑ የዘጌ አናዳ፣ ትክትክ፣ መንጋጋ ቆልፍ (DPT) ክትባት ወስዷል?

Diptheria, Rertussis and Tetanus ማለት ለዘጌ አናዳ፣ ለትክትክና ለመንጋጋ ቆልፍ መከላከያ የሚሆን በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለሦስት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው፡፡ ሕፃኑ የዲ.ፒ.ቲ. /D.P.T/ ክትባት ተደርጎለታል ከተባለ የክትባት ካርዱን በማየት ወይም በመጠየቅ መልሱን "አዎን" ከሆነ ኮድ 1 ይጠቀራል፣ "የለም" የሚል ከሆነ ኮድ 2 ይጠቀራል፡፡

ይህ ክትባት የሚሰጠው በሕፃኑ መቀመጫ ወይም ታፋ በኩል ነው፡፡ የፀረ-6 ክትባት ካርድ ላላቸው ሕፃናት ይህ ክትባት መሰጠቱ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

ማስታወሻ፡- መጀመሪያ ልጁ የD.P.T ክትባት መውሰዱ ይጠየቃል፡፡ ከዚያም በመቀጠል የልጅነት ልምሻ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ መጠየቅ፣ ክትባቱን ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ ብዛቱ ይጠየቃል፡፡

## ሕፃኑ የልምሻ (Polio) ክትባት ወስዷል?

ለልጅነት ልመሻ ( Polio) መከላከያ የሚሆን በተወሰነ የጊዜ ርቀት ለሦስት ጊዜ የሚሰጥ ክትባት ነው፡፡ ሕፃኑ የልጅነት ልምሻ (Polio) ክትባት ተደርጎለት ከሆነ የክትባቱን ካርድ በማየት ወይም በመጠየቅ አረጋግጦ መልሱን በዓምዱ "አዎን" የሚል ከሆነ ኮድ "1" ይጠቀራል፣ "የለም" ካለ ደግሞ ኮድ "2" ይጠቀራል፡፡ የፖሊዮ ክትባት በፈሳሽ መልክ በአፍ የሚሰጥ ሲሆን ከ199ó፣ እስከ 1995 ዓ.ም. ድረስ በጥቅምትና ህዳር ወር በዘመቻ መልክ ሲሰጥ የነበረ እና ከዚያ በፊትም ክትባቱ ይሰጥ እንደነበር መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ማስታወሻ፡- 1. Polio 0 ክትባት የሚሰጠው ሕፃኑ በህክምና ተቋማት ሲወለድ ነው።

2. Polio 1, 2, 3 ደግሞ ህፃኑ በተወለደ በየ4 ወር ልዩነት በአንድ ዓመት ውስጥ የሚጠናቀቅ ክትባት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

3. ህፃኑ የ "Polio 1" ክትባት ሳይወስድ "Polio 2" ክትባት ወይም "Polio 2" ክትባት ሳይወስድ "Polio 3" ክትባት ሊሰጠው እንደማየችል ማስተዋል ያስፈልጋል። ሆኖም "Polio 0" ክትባት ሳይወስድ Polio 1, 2, 3 በተከታታይ ሊሰጠው ይችላል።

## ሕፃኑ የቫይታሚን ኤ (Vit.A) እንክብሎች ወስዷል?

ለቤተሰቡ የቫይታሚን ኤ (Vitamin A) ሁለቱን ዓይነት ናሙና እንክብሎች (ካፕሱሎች) በማሳየት ለሕፃኑ ተሰጥቶ ይታወቅ እንደሆነ በመጠየቅ "አዎን" የሚል ከሆነ ኮድ "1" ይጠቆራል፣ "የለም" ካለ ደግሞ ኮድ "2" ይጠቆራል።

**I.8: Has the child been sick with_____ in the last 2 week? (YOU MAY MARK MORE THAN ONE ANSWER)**

**ተ.8: ህፃኑ በባለፉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ በ ___ ታሞ/ታማ ነበር? (ከአንድ በላይ መልስ ሊጠቆር ይችላል)።**

ህፃኑ በባለፉት ሁለት ወራት ውስጥ በተቅማጥ ወይም በትኩሳት ወይም/እና በሳል ታሞ እንደሆነ እናቱን/አሳዳጊውን በመጠየቅ ታሞ ከሆነ "Y"ን የያዘው ክብ በየአንዳንዱ በሽታ ትይዩ የሚጠቆር ሲሆን ካልታመመ ግን "N" የሚለው ክብ በየአንዳንዱ በሽታ ትይዩ ይጠቆራል።

ማስታወሻ፡- ህፃኑ በተቅማጥ፣ በትኩሳት፣ በሳል/ጉንፋን፣ በሳልና ተቅማጥ፣ በተቅማጥና በትኩሳት፣ በሳልና በትኩሳት ወይም በሦስቱም በሽታዎች ሊታመም እንደሚችል ማስተዋል ያስፈልጋል።

## Section J: Use and satisfaction with facilities and services
## ክፍል ቸ፡ በአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አጠቃቀምና እርካታ

በዚህ ክፍል የሚሰበሰበው መረጃ በጥናቱ የሚሸፈኑት ቤተሰቦች በአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አጠቃቀምና እርካታን በተመለከተ ሲሆን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት ባለፉት 12 ወራት ምን እንደሚመስልም /መሻሻል/ አለመሻሻላቸውንም እንዲሁ ያጠቃልላል፡፡

አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች፡- በዚህ ክፍል 19 ዋና ዋናዋናዎቹ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ተዘርዝረዋል፡፡ ከጥያቄ ሀ እስከ መ ያሉት ጥያቄዎች መረጃ የሚሞላላቸው በዚህ ክፍል በተዘረዘሩት የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት መሠረት መሆን ያለበት ሲሆን የአንዱን የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ጥያቄ ወደ ጎን /እስከ ጥያቄ መ ድረስ/ ከተሞላ በኋላ ወደ ቀጣዩ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት መሄድ ያስፈልጋል፡፡

ጥያቄ A:- **How often do you use this service?**

ጥያቄ ሀ፡- ቤተሰቡ ምን ያህል በአገልግሎት ሰጪው ድርጅት ይጠቀማል?

በዚህ ጥያቄ በአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ስር በተዘረዘሩት የእያንዳንዱ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ቤተሰቡ በድርጅቶቹ ምን ያህል እንደሚጠቀም የሚጠየቅ ሲሆን ለጥያቄው ተስማሚውን መልስ ማጥቆር ያስፈልጋል፡፡ መልሶቹም፡-

| | | |
|---|---|---|
| Not at all | 1 | ምንም አልጠቀምም |
| Occasionally | 2 | አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ |
| Often | 3 | አብዛኛውን ጊዜ እጠቀማለሁ |
| All the time | 4 | ሁልጊዜ እጠቀማለሁ |

ጥያቄ B:- **Main reason for occasional or non-use**

ጥያቄ ለ:- ቤተሰቡ በጥያቄ "ሀ" አልፎ አልፎ እጠቀማለሁ ወይም ምንም አልጠቀምም ካለ ምክንያት፡፡

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ "ሀ" መልስ 1 ወይም 2 ለተሞላላቸው ሲሆን ቤተሰቡ በአገልግሎት ሰጪው ድርጅት ያልተጠቀመበት ዋናው ምክንያት ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ተወስዶ ይጠቆራል፡፡ ቤተሰቡ በተለያዩ ምክንያቶች በአገልግሎት ሰጪው ድርጅት ላይጠቀም ይችላል፡፡ ስለሆነም ከተሰጡት ምክንያቶች ውስጥ ዋናውን ብቻ በመምረጥ ማጥቆር ያስፈልጋል፡፡ አማራጭ ምክንያቶቹም፡-

| | | |
|---|---|---|
| Too far away | 1 | በጣም ሩቅ ስለሆነ |
| Too expensive | 2 | በጣም ውድ ስለሆነ |
| Poor Service | 3 | አገልግሎት አሰጣጡ ደካማ ስለሆነ |
| No staff/equipment | 4 | ሠራተኛ/መሣሪያ ስለሌለው |
| Inadequate facilities | 5 | አገልግሎት የተሟላ ባለመሆኑ (ዕቃዎች፣ ሠራተኞች ...ወዘተ) |
| Other | 6 | ሌላ |
| Not applicable | 7 | ስለማይመለከተው:: |

በመሆኑም በጥያቄ "ሀ" አማራጭ /ኮድ/ ምክንያት "3" ወይም "4" ከተጠቆረ ይህ ጥያቄ ይታለፋል (ምንም ነገር አይጠቆርበትም)::

ጥያቄ "C" :- How Satisfied are you with the quality of service?

ጥያቄ "ሐ":-ቤተሰቡ ባገኘው አገልግሎት ምን ያህል ረክቷል/ተደስቷል/

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ "ሀ" ኮድ 2 /አልፎ አልፎ/፣ ኮድ 3/ አብዛኛውን ጊዜ/ወይም ኮድ 4/ሁልጊዜ/ እጠቀማለሁ ተብሎ ለተሞላላቸው የአገልግሎት ዓይነቶች ሲሆን ቤተሰቡ አገልግሎት ባገኘባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች መርካት /መደሰት/ ወይም አለመርካቱ/አለመደሰቱ/ ተጠይቆ አልረካሁም /አልተደሰትኩም/ ካለ ኮድ፣ ረክቻለሁ/ተደስቻለሁ/ ካለ ደግሞ ኮድ 2 ተመርጦ መጠቆር ይኖርበታል:: ነገር ግን ለጥያቄ "ሀ" ኮድ 1 ከተጠቆረ በዚህ ጥያቄ ምንም ነገር አይፃፍለትም-አይጠቆርም::

ጥያቄ "D":- How has the quality of service changed in the last 12 months?

ጥያቄ "መ":-ቤተሰቡ ባለፉት 12 ወራት በአገልግሎት ሰጪ.ው ድርጅት ያገኘው አገልግሎት ምን ዓይነት ለውጥ አሳይቷል?

ይህ ጥያቄ የሚጠየቀው በጥያቄ "ሀ" ኮድ 2፣ 3 ወይም 4 ለተሞላላቸው በአገልግሎት ሰጪ. ድርጅቶች ለተጠቀሙ ቤተሰቦች ነው:: ስለሆነም ባለፉት 12 ወራት ከአገልግሎት ሰጪ. ድርጅቶች ያገኘው አገልግሎት አሁን ካለው ጋር በማወዳደር የሚጠየቅ ሲሆን የሚሰጠውን መልስ ከተሰጡት አማራጭ መልሶች ጋር በማገናዘብ/በማዛመድ ማጥቆር ያስፈልጋል:: አማራጭ መልሶችም:-

| | | |
|---|---|---|
| Worse now | 1 | አሁን መጥፎ ነው |
| Same as before | 2 | ከበፊቱ ለውጥ የለውም |
| Better now | 3 | አሁን ደህና ነው/ ከበፊቱ ይሻላል |
| Don't know | 4 | አላውቅም |

ማስታወሻ:- በጥያቄ "ሀ" ኮድ 1 ከተሞላ በዚህ ጥያቄ "መ" ምንም ነገር አይጠቆርም (ባዶ ይታለፋል)::

## A.8 Result

## ሀ.8 ውጤት

በዚህ ክፍል መረጃ ሰብሳቢው መጠይቁን የሚሟላበት ወቅት ያጋጠመውን ችግር መኖር አለመኖሩን ለማወቅ የሚስችሉ መረጃዎችዕ ለማስገኘት የሚረዳ ስለሆነ ከተጠቀሱት 3 ምርጫዎች መካከል አንዱን አማራጭ በመምረጥ ከፊት ለፊት የተሰጠው ክብ/ኮድ ይጠቆራል::

| | | |
|---|---|---|
| Complete with selected household | 1 | ለጥናቱ የተመረጠው ቤተሰብ ያለምንም ችግር በመጠየቅ መጠይቁ ተሞልቷል |
| Complete with replacment refusal | 2 | መጠይቁ የተመረጠው ቤተሰብ ተቃውሞ ምክንያት ተተክቶ ተሰርቷል |
| Complete with replacemnent not found | 3 | መጠይቁ በተመረጠው ቤተሰብ መጥፋት ምክንያት ተተክቶ ተሠርቷል |

## A.9 Interview End

## ሀ.9 የጥያቄ መጨረሻ

በዚህ ጥያቄ መረጃ ሰብሳቢው የአንዱን ቤተሰብ መረጃን ለመሙላት ምን ያህል ጊዜ/ሰዓት እንደሚወስድበት ለማወቅ የሚረዳው መረጃ የሚያስገኘው ሲሆን መረጃ ሰብሳቢው መረጃ መሰብሰብ ሲጀምር ስንት ሰዓት እና ደቂቃ እንዲሁም በቀን ወይም በማታ እንደሰራው በጥያቄ ሀ.5 የተጠየቀለት ሲሆን በዚህ ጥያቄ ደግሞ መረጃ ሰብስባቢውን በቅፅ [illegible] ጥያቄዎች በሙሉ አጠናቆ ሲጨርስ የነበረው ሰዓትና ደቂቃ እንዲሁም የተሞላው ሰዓት ማታ ወይም ቀን መሆኑን ለማሳየት ቀን ከሆን " D" የሚለው ክብ ሲጠቆር ማታ ከሆነ ደግሞ " N" የሚለው ክብ ይጠቆራል::